# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

ግሩም ጥበቡ

ከበደ አየለ

**አርታኢዎች**

እሸቱ አጋ

አንበሴ በቀለ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

በርናባስ ደበሎ

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ እና ምሥል ገለጻ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© 2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ።

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የስዕሎችን የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# አማርኛ

## ማውጫ


መቅድም ..... iv

መግቢያ ..... vi

ምዕራፍ አንድ፡ ጤና ..... 1

ምዕራፍ ሁለት፡ ጎረቤታሞች ..... 1

ምዕራፍ ሶስት፡ ስነቃል ..... 1

ምዕራፍ አራት፡ የጊዜ አጠቃቀም ..... 1

ምዕራፍ አምስት፡ መጓጓዣ ..... 1

ምዕራፍ ስድስት፡ ስነምግባር ..... 1

ምዕራፍ ሰባት፡ ግብርና ..... 1

ምዕራፍ ስምንት፡ ስራ ..... 1

ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ባህል ..... 1

ምዕራፍ አስር፡ ገበያ ..... 1

## መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለውን ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ትኩረት በመስጠት አዲስ ስርዓተ ትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። አዲሱን ስርዓተ ትምህርት ቀርጾ ከማቅረቡ በፊት ግን ቀደም ሲል ስራ ላይ የነበረውን መመርመርና የተስተዋሉ ችግሮችን ነቅሶ ማውጣት ተገቢ ነበር:: ይህንን ለማሳካት በተደረገው ጥናትም ቀድሞ ስራ ላይ የነበረው ስርዓተ ትምህርት የተለያዩ ክፍተቶች ተገኝተውበታል:: ከነዚህም መካከል የተማሪዎቹን ደረጃ የመጠነ አለመሆኑ፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለማድረጉ፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠኑ እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀሙ ይጠቀሳሉ። ስለሆነም የተማሪዎችን የአፍመፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ ትምህርቱን በአውድ የተደገፈ ለማድረግ፣ እና በመማር ላይ የተመሰረተ ትምህርታዊ ስኬታማነትን ለማረጋገጥ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት እንዲቀረጽ ሆኗል።

በአዲስ መልክ የተቀረጸውን ስርዓተ ትምህርት መሠረት በማድረግም የትምህርት መሳሪያዎቹ ተዘጋጅተዋል። የተማሪ መማሪያ መጽሐፍም ከመሳሪያዎቹ አንዱ እንደመሆኑ መጠን ይህ የአማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

# አማርኛ

በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሊዘጋጅ ችሏል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን አነስተኛ የመማር ብቃቶች (Minimum Learning Competencies)፣ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች እንዲሁም ተግባቦታዊ የመማር ዘዴዎችን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው።

ከዚህ አንፃር የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በቀድሞው የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል።

## መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች አሉት። እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በስሩ አምስት ንዑሳን የትምህርት ክፍሎችን አካቷል። እነዚህም ትምህርት ክፍል አንድ ‘ማዳመጥ’፣ ትምህርት ክፍል ሁለት ‘መናገር’፣ ትምህርት ክፍል ሶስት ‘ማንበብ’፣ ትምህርት ክፍል አራት ‘ቃላት’፣ ትምህርት ክፍል አምስት ‘መጻፍ’ እና ‘ሰዋስው’ (የሰዋስው ትምህርቱ በተናጠል ባይቀርብም) ናቸው። እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል በመርሃ ትምህርቱ በተደለደለው መሰረት በክፍለጊዜ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በስሩ መመሪያዎች፣ ትዕዛዛት፣ መልመጃዎች እና ተግባራትን አካቷል። ከዚህ አኳያ መሰረታዊ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመ ተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረ ተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ነው። የቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ማቅረቢያ ዘዴን ተከትለዋል። ከዚህ በመነሳትም የዚህ መማሪያ መጽሐፍ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

# ምዕራፍ አንድ፡ ጤና

ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል 'ጤናማና ደስተኛዋ ደራርቱ' የሚል ፅሑፍና መልመጃዎች ስለቀረቡ በሚሰጣችሁ ትዕዛዝ መሰረት በትኩረት ስሩ።**

### ጤናማና ደስተኛዋ ደራርቱ



### የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. ፅዳታችሁን እንዴት ትጠብቃላችሁ?
2. ጤናማ ሆናችሁ ለመገኘትስ ምን ታደርጋላችሁ?

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።**

1. ደራርቱ በሰፈሯ የምትታወቀው በምንድን ነው?
2. ደራርቱ ንፅህናዋን ለምን ትጠብቃለች?
3. የደራርቱ ተወዳጅነት ከምን የመነጨ ነው?
4. ካዳመጣችሁት ታሪክ ምን ተማራችሁ?
5. እናንተ ተወዳጅ ለመሆን ምን ማድረግ አለባችሁ?

ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### መልመጃ ሁለት

**ለሚከተሉት ቃላት ባዳመጣችሁት ፅሑፍ መሰረት ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ አረፍተ ነገር መስርቱ።**

*ምሳሌ፡ ጤናማ = በሽታ የሌለበት ሰው*

*አረፍተ ነገር፡ ጤናማ ልጅ ደስተኛ ይሆናል።*

| | | |
|---|---|---|
| ተወዳጅነት | ንፅህና | ደስተኛ |
| የተመጣጠነ | ጤናማ | ተዋፅኦዎች |

ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

አንድ ሰው ጤና አጣ የሚባለው ምን ሲሆን እንደሆነ በቡድናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ በተወካያችሁ አማካኝነት የቃል ዘገባ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር ሁለት

ጤናማ ያልሆነ ሰው ምን ምን ችግሮች እንደሚያጋጥሙት በመጀመሪያ የአካባቢያችሁን ሰዎች ጠይቁ:: በመቀጠል ያገኛችሁትን መረጃ አደራጁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### የተመጣጠነ ምግብ



## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. *ከላይ በምስሉ ከቀረቡት የምግብ አይነቶች የትኞቹን ታውቃላችሁ? ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።*
2. *ለመኖር የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?*

ለሰው ልጆች ጤና ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ የምግብ አይነቶች አሉ። እነዚህም ሀይል ሰጪ፣ ሰውነት ገንቢ እና ከበሽታ ተከላካይ ይባላሉ።

ሀይል ሰጪ ምግቦች ሰውነታችን የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውን አቅም ይሰጡታል። ድንች፣ ዳቦ፣ ማር፣ ፓስታ፣ መኮሮኒ፣ የሸንኮራ አገዳ ሀይል ሰጪ ናቸው።

1. ከአንቀፅ ‘1’ እና ‘2’ ምን ተረዳችሁ?
2. ቀጣዩ የምንባቡ ክፍል ስለምን የሚነግረን ይመስላችኋል?

በሌላ በኩል ለሰውነታችን እድገት ገንቢ ምግቦች ያስፈልጋሉ። በተለይ ለህፃናትና ነፍሰ ጡር እናቶች ገንቢ ምግቦች ጠቃሚ ናቸው። ለአብነትም ስጋ፣ እንቁላል፣ ወተት፣ ኦቾሎኒ ይጠቀሳሉ።

በመጨረሻም ሰውነታችን ከበሽታ የሚከላከሉ ምግቦች ያስፈልጉታል። እነዚህም አትክልትና ፍራፍሬዎች ናቸው። ቲማቲም፣ ቃሪያ፣ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቆስጣ አትክልቶች ሲሆኑ፣ ብርቱካን፣ ፓፓያ፣ ማንጎ፣ አናናስ የመሳሰሉት ደግሞ ፍራፍሬዎች ናቸው።

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

**ሀ. በምንባቡ መሰረት እየተወያያችሁ መልሱ።**

1. የአንቀፅ ሁለት ፍሬ ነገር ምንድን ነው?
2. አንቀፅ ሦስት ስለየትኛው የምግብ አይነት ያስረዳል?
3. አንቀፅ አራት የሚነግረን ስለምንድን ነው?
4. ከሀይል ሰጪ የምግብ አይነቶች ሦስት ጥቀሱ።
5. ከተጠቀሱት የምግብ አይነቶች ለሰውነት ጠቃሚ የሆኑት የትኞቹ ናቸው? ለምን?

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

**ለ. በ ‘ሀ’ ስር የቀረቡትን የምግብ አይነቶች በ ‘ለ’ ስር ካሉ ምሳሌዎቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሀይል ሰጪ | ሀ. ቃሪያ፣ ካሮት፣ ብርቱካን |
| 2. ሰውነት ገንቢ | ለ. ዳቦ፣ ድንች፣ ፓስታ |
| 3. በሽታ ተከላካይ | ሐ. ስጋ፣ ወተት፣ እንቁላል |

**ሐ. ትክክለኛውን መልስ ስጡ።**

1. እንቁላል፣ ወተትና ስጋ በየትኛው የምግብ አይነት ውስጥ ይመደባሉ?
2. በሽታ ተከላካይ የምግብ አይነት የሆኑትን ዘርዝሩ?
3. ነፍሰ ጡር እናቶችና ህፃናት የትኞቹ የምግብ አይነቶች በብዛት ያስፈልጓቸዋል?

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

### ተግባር ሦስት

**ቀጥሎ የቀረቡላችሁን አረፍተነገሮች ድምፅ እያሰማችሁ ተራ በተራ አንብቧቸው።**

1. ጤናማ ሆነው የሚኖሩ ሰዎች ስራቸውን በአግባቡ ይሰራሉ።

2. ሰዎች የተበላሸ ምግብ ከተመገቡና አካላዊ እንቅስቃሴ ካላደረጉ ይታመማሉ።

3. ሙዝ፣ ማንጎ፣ ብርቱካን፣ መንደሪንና አናናስ የፍራፍሬ አይነቶች ናቸው።

4. እንስሳት የቤትና የዱር ተብለው ይከፈላሉ። የቤት እንስሳት ከሰዎች ጋር የሚኖሩ ሲሆን፣ የዱር እንስሳት ደግሞ በጫካ ይኖራሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስር

### ተግባር አራት

**ቀጥሎ የቀረበላችሁን አንቀፅ ተራ በተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ። በማንበብ ሂደት ወቅትም ጓደኞቻችሁ በትክክል ያላነበቧቸውን ቃላት መዝግቡ።**

ቆሻሻ ደረቅ ወይም ፈሳሽ በሆነ መልኩ ሊገኝ ይችላል። ይህንን በተለያየ መልክ የሚገኝ ቆሻሻም ማስወገድ ይገባል። ቆሻሻ የሚወገድባቸው መንገዶች የተለያዩ ናቸው። ከነዚህ መካከል ቆሻሻን ማቃጠልና ጉድጓድ ቆፍሮ መቅበር ዋነኞቹ ናቸው። ቆሻሻ በአግባቡ ካልተወገደ ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል፤ ለወረርሽኝ መከሰትም ምክንያት ይሆናል። ስለዚህ ቆሻሻን በአግባቡ እናስወግድ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ አራት

**ሀ. በ ‘ሀ’ ስር የተሰጡትን ቃላት በ ‘ለ’ ስር ከቀረቡ ፍቺዎቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እንዳይጠቃ | ሀ. ተመሳሳይ ያልሆኑ |
| 2. የተለያዩ | ለ. ከጉዳት የሚጠብቁ |
| 3. ተከላካይ | ሐ. የሚመደቡ/የሚጨመሩ |
| 4. የሚካተቱ | መ. ጉዳት እንዳይደርስበት |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

### ተግባር አምስት

**በአካባቢያችሁ ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ አይነቶችን ዘርዝሩ። በመቀጠልም የምግብ አይነቶቹን በየምድባቸው አስቀምጧቸው::**

**ምሳሌ፡**

| ከእንስሳት የሚገኙ | ከእህል ዘሮች የሚገኙ | አትክልት የሆኑ | ፍራፍሬ የሆኑ |
|---|---|---|---|
| ስጋ | እንጀራ | ዱባ | ማንጎ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

### መልመጃ አምስት

**በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

**ምሳሌ፡** ሀ. ዘምዘም ከህመሟ **አገገመች**።

**አገገመች**፡ ተሻላት ወይም ዳነች

ለ. ጀቤሳ በጥንቃቄ **የተዘጋጀ** ምግብ ይመገባል።

**የተዘጋጀ**፡ *የተሰራ ወይም የተሰናዳ*

1. የታመመ ሰው በሀኪም የታዘዘለትን መድሃኒት **መውሰድ** አለበት።
2. ጥርሳችንን ሁልጊዜ በአግባቡ **ማፅዳት** ይገባናል።
3. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ሰውነትን **ያጎለብታል**።
4. ህፃናት በጥንቃቄ ካልተጫወቱ ለ**ጉዳት** ይዳረጋሉ።
5. በቫይታሚን **የበለፀጉ** ምግቦች ከበሽታ ይከላከላሉ።
6. እህቴ በሽታው **ስላገረሸባት** ሆስፒታል ተወሰደች።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ስድስት

**በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት እየመረጣችሁ ቀጥለው የቀረቡ አረፍተነገሮችን አሟሉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ተገቢ | መመገብ | እንዳንጠቃ |
| ሲታመሙ | አቀዝቅዞ | መሠረታዊ |

1. ምግብ አንዱ የሰው ልጅ _______ ፍላጎት ነው።
2. የተበላሹ ምግቦችን ______ ለበሽታ ያጋልጣል።
3. ውሃን አፍልቶና ______መጠጣት ጠቃሚ ነው።
4. ወላጆች ልጆች _____ ወደ ጤና ጣቢያ ይወስዳሉ።
5. በትንፋሽ በሚተላለፍ በሽታ ______ አፍ እና አፍንጫችንን እንሸፍን።
6. እጅን ሳይታጠቡ መመገብ _______ አይደለም።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ሰባት

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች በትክክለኛው ቅደም ተከተላቸው መልሳችሁ ጻፏቸው።**

1. ከጓደኞቼ ጋር ሰላምታ ተለዋወጥን።
2. በጥዋት ከእንቅልፌ ነቃሁ።
3. በክፍል ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ አደረኩ።
4. መማሪያዎቼን ይዤ ትምህርት ቤት ሄድኩ።

5. እጁንና ፊቱን ታጥቤ ቁርሴን በላሁ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስምንት

**የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።**

| | | |
|---|---|---|
| መታከም | ህመምተኛ | ማገገም |
| በሽታ | ጤናማነት | |

**ምሳሌ፡ መታከም**

የታመመ ሰው ሀኪም ቤት ሄዶ መታከም አለበት።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ ዘጠኝ

**በሰንጠረዡ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በማገጣጠም የተሟላ አረፍተ ነገር መስርቱ።**

ምሳሌ፡ ሁሴን ክፍሉን አፀዳ።

| | | |
|---|---|---|
| ቀጄላ | ሀሳቧን | ሄዱ። |
| ትዕግስት | መፅሐፍ | አመጣች። |
| ሶፊያና ደራርቱ | ክፍሉን | አካፈለች። |
| ሁሴን | ተማሪ | ነኝ። |
| እኔ | ድሬዳዋ | አፀዳ። |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### ተግባር፡ ስድስት

**ቀጥሎ የቀረቡትን ስዕሎች በማየት አጫጭር አረፍተነገሮች ፃፉ።**




ምሳሌ፡ ኮረና በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት፡ ጎረቤታሞች

ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል የማዳመጥ ክሂላችሁን እንድታሻሽሉ የሚረዷችሁ ተግባራትና መልመጃዎች ቀርበዋል። በትዕዛዛቱ መሰረት ሁሉንም ስሩ።

### ተሊሌና አበበች

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄ

ከነዚህ ቃላት የትኞቹን ታውቃላችሁ?

| ጎረቤት | መንደር | ይቅርታ | ማስታረቅ |
|---|---|---|---|

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

#### መልመጃ አንድ

ቀደም ሲል ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ተከታዮቹን ጥያቄዎች 'እውነት' ወይም 'ሀሰት' በማለት መልሱ። ምክንያታችሁንም በቃል አስረዱ።

1. አበበችና ተሊሌ በወቅቱ ጓረቤታሞች አልነበሩም::

2. ተሊሌና አበበች ቤተሰቦቻቸውን አጣልተው ነበር።
3. የአበበችና የተሊሌ ቤተሰቦች ባጠፉት ተፀፅተዋል።
4. ተሊሌና አበበች በትምህርት ጎበዞች አልነበሩም።
5. አዛውንቱ የተጠሩት የተጣሉትን ለማስታረቅ ነው።
6. ልጆቹ ቤተሰቦቻቸው በመታረቃቸው ተደስተዋል።

ክፍለጊዜ፡ ሦስት

## መልመጃ ሁለት

**ሀ. በ 'ሀ' ስር ያሉትን ቃላት በ 'ለ' ስር ከተዘረዘሩት አውዳዊ ፍቺያቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መንደር | ሀ. የዕድሜ ባለ ፀጋ፣ ሽማግሌ |
| 2. ባልተገባ | ለ. አንድ ላይ ሆነን፣ አብረን |
| 3. ተኮራርፈው | ሐ. አሳመኑ፣ እሺ አስባሉ |
| 4. ተከፉ | መ. ተስማሙ፣ መጣላት አበቃ |
| 5. ተነጋገሩ | ሠ. ሳይነጋገሩ፣ ሳያወሩ |
| 6. ተያይዘን | ረ. ልክ ባልሆነ፣ በማይሆን |
| 7. አዛውንት | ሰ. የመኖሪያ አካባቢ፣ ሰፈር |
| 8. አግባቡ | ሸ. ተወያዩ፣ ተመካከሩ |
| 9. እርቅ አወረዱ | ቀ. አዘኑ፣ ሳይመቻቸው ቀረ |

### ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

**ቤተሰባችሁን ወይም በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎችን በጉርብትና ሲኖሩ ስላጋጠሟቸው ነገሮች በመጠየቅ ቀጥሎ በቀረቡት ነጥቦች ላይ የቃል ዘገባ አቅርቡ።**

- አለመግባባቶች ተፈጥረው ያውቁ እንደሆነ፣
- እርቅ እንዴት እንደሚወርድ…

### ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የተጣሉ ሰዎች ሲያጋጥሙን ምን ማድረግ አለብን?
2. ቤተሰቦች ከተጣሉ ልጆችም መጣላት ያለባቸው ይመስላችኋል? ለምን?
3. አንድ ጓደኛችሁ ታሞ ቢተኛ ምን ታደርጋላችሁ?
4. ጎረቤታሞች ሳይጣሉ ለመኖር ምን ምን ማድረግ አለባቸው?

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### መልመጃ ሦስት

**ተማሪዎች ቀጣዩን ምንባብ በአንቀፅ በአንቀፅ ተከፋፍላችሁ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡ።**

የኮሮና በሽታ ወይም ኮቪድ 19 አዲስ በተከሰተ ቫይረስ አማካኝነት የሚተላለፍ ወረርሽኝ ነው። ኮቪድ 19 ሁሉንም የአለም ክፍል ያዳረሰ ሲሆን፣ ማንኛውንም የህብረተሰብ ክፍል ያጠቃል። በኮቪድ 19 የተጠቁ ሰዎች ከቀላል እስከ ከባድ የመተንፈሻ አካላት ህመም ይጋለጣሉ። ብዙዎቹም የተለየ የህክምና አገልግሎት ሳያገኙ አገግመዋል። ይሁን እንጂ በእድሜ የገፉና ተጓዳኝ በሽታ ያለባቸው በርካታ ግለሰቦች ህይወታቸውን አጥተዋል።

የኮረና ቫይረስ የሚተላለፈው በትንፋሽ አማካኝነት ሲሆን፣ ማስነጠስ፣ ማሳልና አካላዊ ንክኪ በሽታውን አዛምተዋል። ለበሽታውም እስካሁን ፍቱን መድሃኒት አልተገኘለትም። እጅን ደጋግሞ በሳሙና መታጠብ፣

አካላዊ ርቀት መጠበቅ፣ የእጅ ማፅጃ ኬሚካል መጠቀምና አፍና አፍንጫን መሸፈን ጠቃሚ መከላከያ መንገዶች ናቸው።

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## መልመጃ አራት

**ተከታዩን ምንባብ በየግላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።**



## ጉርብትና

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ስዕሉን በተመለከተ ያስተዋላችሁትን ለጓደኞቻችሁ አስረዱ።
2. ስለጎረቤቶቻችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

ጉርብትና መኖሪያቸውን ጎን ለጎን ያደረጉ ሰዎች የሚመሰርቱት ነው። ጉርብትና ማህበራዊ ህይወትን

ከማስጀመሪያ መንገዶች አንዱ ነው። በዚህም ሰዎች በደስታቸውና በሀዘናቸው ወቅት ግንኙነታቸውን ያጠናክሩበታል። ጥሩ ጉርብትና የሚባለው መከባበር፣ መቻቻልና መተማመን ያለበት ነው።

1. ጉርብትና መኖሪያቸውን ___________ ያደረጉ ሰዎች የሚመሰርቱት ነው።
2. ጥሩ ጉርብትና የሚባለው __________፣ __________ እና __________ ያለበት ነው።

ጥሩ ጉርብትና ያላቸው ሰዎች ደስ የሚል ማህበራዊ ህይወት ይኖራቸዋል። አካባቢያቸውንም ተወዳጅና ተናፋቂ ማድረግ ይችላሉ። በስራ ይተጋገዛሉ፣ በዓላትን አብረው ያከብራሉ፣ በችግር ጊዜም ይረዳዳሉ።

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አምስት

**በምንባቡ መሰረት ተገቢውን መልስ ስጡ።**

1. ጉርብትና እንዴት ይመሰረታል?
2. ጎረቤቶች ጥሩ ናቸው የሚባሉት ምን ምን ተግባራትን ሲያከናውኑ ነው?
3. ጥሩ ጎረቤት ያልሆኑ ሰዎች በምን ይታወቃሉ?
4. ደስ የሚል ማህበራዊ ህይወት የሚመሰረተው እንዴት ነው?

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ተግባር ሦስት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተመለከተ መረጃ ሰብስቡ፤ ያገኛችሁትን መረጃም በፅሑፍ አደራጁ፤ ፅሑፉን ክፍል አምጥታችሁ ለጓደኞቻችሁ እያነበባችሁ ተወያዩበት።**

1. ከጎረቤት ጋር መኖር ስላለው ጠቀሜታ
2. ያለጎረቤት መኖር ስለሚያመጣው ጉዳት

ክፍለጊዜ፡ አስር

## መልመጃ ስድስት

**ትክክለኛውን ምላሽ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. ሰዎች በደስታቸውና በሀዘናቸው ወቅት ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩበት _______ ነው።

ሀ. ቤት ለ. ሰፈር ሐ. ጉርብትና መ. ዘመድ

2. መከባበር፣ መቻቻልና መተማመን ያለበት ጉርብትና _______ ይባላል።

ሀ. መጥፎ ጉርብትና ለ. ጥሩ ጉርብትና

ሐ. የነገር ጉርብትና መ. የመኳረፍ ጉርብትና

3. መልካም ጉርብትና ያላቸው ሰዎች ደስ የሚል _______ ይኖራቸዋል።

ሀ. ግላዊ ህይወት ለ. ሀሳባዊ ህይወት

ሐ. ምድራዊ ህይወት መ. ማህበራዊ ህይወት

4. ጥሩ ጎረቤት በችግር ጊዜ _______

ሀ. ይረዳዳል ለ. አይረዳዳም

ሐ. ዝም ይላል መ. ምንም አያደርግም

5. ከሚከተሉት አንዱ ጥሩ ጎረቤታሞች ማድረግ የሚገባቸው አይደለም።

ሀ. መከባበር ለ. መረዳዳት

ሐ. መጨቃጨቅ መ. መተዛዘን

ክፍለጊዜ፡ አስር

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ ሰባት

**ሀ. በምንባቡን መሰረት ለተከታዮቹ ቃላት ፍቺ ስጡ።**

**ምሳሌ፡ ጎን ለጎን ⟶ አጠገብ ለአጠገብ፣ በመደዳ**

| | | |
|---|---|---|
| መንገዶች | መከባበር | ይተጋገዛሉ |
| ግንኙነታቸውን | ተናፋቂ | |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ


### ለ. በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት እየመረጣችሁ አረፍተ ነገሮቹን አሟሉ።

| | | |
|---|---|---|
| መተጋገዝ | መተሳሰብ | ጎረቤት |
| ወዳጅነትን | መመስረት | ምቹ |

1. ጉርብትናን <u>መመስረት</u> በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።
2. በማህበረሰባችን ዘንድ በስራ ወቅት _______ የተለመደ ነው።
3. በችግርም ሆነ በደስታ ጊዜ ________ ደራሽ ነው።
4. ሰፈራችን ለኑሮ ________ የሆነ ቦታ ነው።
5. ሰዎች በፍቅር አብረው ሲኖሩ ________ ያፈራሉ።
6. አብሮ በመኖር ወቅት መቻቻልና ________ ያስፈልጋል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት





ሐ. በ 'ሀ' ስር ያሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ተቃራኒያቸውን ከ'ለ' ስር በመፈለግ አዛምዱ።

ምሳሌ፡

መጣላት → መታረቅ

ሆድ → ጀርባ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መቻቻል | ሀ. መጀመር |
| 2. ወዳጅ | ለ. ጥላቻ |
| 3. መጣላት | ሐ. ሩቅ |
| 4. ፍቅር | መ. መታረቅ |
| 5. መጠናቀቅ | ሠ. መገፋፋት |
| 6. ቅርብ | ረ. ጠላት |

መ. ከሳጥኑ ውስጥ በመምረጥ ከየአረፍተነገሮቹ ጎን ፃፉ። በምሳሌነት የመጀመሪያው ተሰርቷል።

| የቃላት ሳጥን | | | |
| --- | --- | --- | --- |
| መቀስ | ኩንታል | ቴሌቪዥን | |
| መፅሐፍ | ብዕር | ጤፍ | ሰረገላ |

1. ብዙዎች በባህላዊ ማጓጓዣነቱ ያውቁታል። ሰረገላ
2. ዜና፣ፊልምና የተለያዩ ዝግጅቶችን እናይበታለን።
3. እህል ለመያዣነትና ለመስፈሪያነት ያገለግላል።
4. አንብበን እንዝናናበታለን፤እውቀት ይቀሰምበታል።
5. ስሜታችንና አመለካከታችንን በወረቀት ላይ እናሰፍርበታለን።
6. ይፈጫል፣ ይቦካል እንጀራ እንዲሆን ይጋገራል።
7. ለመቁረጫነት እና ቅርፅ ለማውጫነት ያገለግላል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

ሠ. ለተሰመረባቸው ቃላት ተቃራኒያቸውን ምረጡ።

1. ጉርብትና የማህበራዊ ህይወት መሰረት ነው።

   ሀ. ሰዋዊ ለ. ግላዊ ሐ. ቡድናዊ መ. ወዳጃዊ

2. <u>**አዲሱ**</u> ቤታችን በጣም ያምራል።

ሀ. ትልቁ   ለ. ትንሹ   ሐ. አሮጌው   መ. ጠባቡ

3. ሶርሳ <u>**ክረምት**</u> ሲደርስ ቤተሰቡን ይጎበኛል።

ሀ. በጋ   ለ. እረፍት   ሐ. እርሻ   መ. ፀሐይ

4. <u>**ከተማ**</u> ግርግር ቢኖርበትም ሰዎች ይወዱታል።

ሀ. ህንፃ   ለ. ጎጆ   ሐ. መኪና   መ. ገጠር

5. <u>**ቁጥቋጦዎች**</u> በረሃማ በሆኑ አካባቢዎች ይበቅላሉ።

ሀ.ተክሎች   ለ.ዛፎች   ሐ. አበባዎች   መ.ችግኞች

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

**መልመጃ ስምንት**

**ቀጣዮቹን አረፍተነገሮች ደብተራችሁ ላይ ፃፉና 'ኦች' የተቀጠለባቸውን ስሞች አስምሩባቸው።**

**ምሳሌ፡** ደቻሳ አስር <u>**ላሞች**</u> አሉት።

1. መስከረም አዳዲስ ልብሶች ገዛች።
2. ተክሎች እንክብካቤ ይፈልጋሉ።
3. ሊበን ብዙ መፅሐፎች አነበበ።
4. አቶ መሐመድ የዛፍ ችግኞች ተከሉ።

5. አበቦች በየመንገዱ ፈክተው ይታያሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ዘጠኝ

ሀ. ከዚህ በታች የተሰጡትን ቃላት ስሜት በሚሰጥ መልኩ እያስማማችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡ (እሱ ፣ጎረቤት ፣እኔ)

<u>እሱ የእኔ ጎረቤት ነው።</u>

1. (እህቴ ፣ታመመ፣ ጠየቀ)
2. (እኔ፣ቁርስ፣ በላ)
3. (አባት፣ ተረት፣ ነገረ)
4. (ሶፊያ፣ ትምህርት፣ ጎበዝ)
5. (እናት፣ ሐኪም፣ መሆን)

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### ስርዓተ ነጥቦች

? ። ፣ " " !

## መልመጃ አስር

**ለ. ተከታዮቹን አረፍተነገሮች ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም መልሳችሁ ፃፏቸው።**

**ምሳሌ፡**

*ለምን ወደ ትምህርት ቤት አብረን አንሄድም?*

*ሀና፣ ሊያንቱና አስቴር ጎረቤታሞች ናቸው።*

1. ስምሽ ማን ነው
2. ብርሃኔ ሁለት እህቶችና አንድ ወንድም አላት
3. ጎበና ግርማና ቶለሺ የክፍል ጓደኞቼ ናቸው
4. ብርቱካን ሎሚ ማንጎና ፓፓያ እዚህ ይገኛሉ
5. በእረፍት ቀንሽ ዘመድ ለመጠየቅ አስበሻል

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## መልመጃ አስራ አንድ

**በሳጥኑ ውስጥ የተሰጧችሁን ፊደላት በመጠቀም የቃል ክፍላቸው ስም የሆኑ ቃላትን መስርቱ።**

**ምሳሌ፡** *ልብስ፣ ገዳ፣ ተማሪ፣ ሀገር...*

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ም | ሌ | ስ | ብ | ሳ | ል | ሎ | ቆ |
| ጥ | በ | ኗ | ቱ | ደ | ር | ን | ካ |
| ሚ | ተ | ዳ | ሪ | ገ | አ | ገ | ት |
| ባ | ክ | ማ | ጌ | | | | |

# ምዕራፍ ሶስት፡ ስነቃል

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ


**ተማሪዎች በዚህ ክፍል 'አንበሳና ሰጎን' የተሰኘ ምንባብ ቀርቦላችኋል። ምንባቡን ተከትሎ የቀረቡትን ተግባርና መልመጃዎች በትዕዛዛቱ መሰረት ስሩ።**

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. ተከታዮቹን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።**

1. ከቤተሰባችሁ ተረት የሚነግራችሁ ማነው?
2. ስለአንበሳና ሰጎን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

## አንበሳና ሰጎን



ስዕል አንድ



ሥዕል ሁለት



ሥዕል ሦስት



ሥዕል አራት

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

1. በጉርብትና አብረው ይኖሩ የነበሩት ባለታሪኮች እነማን ናቸው?
2. ባለታሪኮቹ ያልተስማሙት በምን ጉዳይ ነበር?
3. ቀድመው የተሰበሰቡት እንስሳት እነማን ናቸው?

4. እንስሳቱ ምን ብለው ፈረዱ? ፍርዱ ተገቢ ነበር?
5. ዘግይታ የመጣችው እንስሳ ማን ናት?
6. ለመዘግየቷ ያቀረበችው ምክንያት ምን ነበር?
7. የአንበሳው ስራ አግባብ ነበር ትላላችሁ? ለምን?
8. ከታሪኩ ምን ተማራችሁ? እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

## መልመጃ ሁለት

**ሀ. 'እውነት' ወይም 'ሐሰት' በማለት መልሱ።**

1. ጎረቤታሞች የተባሉት በሬውና ላሚቷ ናቸው።
2. አንበሳ ከብቶች ሲኖሩት ሰጎን ግን አልነበራትም።
3. ሁሉም የዱር እንስሳት ለዳኝነቱ ተጠርተዋል።
4. ጥጃውን የወለደችው ሰጎን መሆኗ ይታወቅ ነበር።
5. ጠጣ መሬት ተሰንጥቃ መስፋቷ ሐሰት ነበር።
6. በውሸት የመሰከሩት እንስሳት በሙሉ አፍረዋል።

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

**ተግባር አንድ**

**ታሪኩን መልሳችሁ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተራችሁን እየጠበቃችሁ ተናገሩ።**

ክፍለጊዜ፡ አምስት

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. የሚከተሉትን ቃላት ከፍቺያቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መመካከር | ሀ. ቶሎ አለመምጣት |
| 2. መፍረድ | ለ. ጭንቅላትን መድፋት |
| 3. መዘግየት | ሐ. ምን እናድርግ ማለት |
| 4. ማቀርቀር | መ. ለመቀበል መቸገር |
| 5. አለማመን | ሠ. ከቦታ ቦታ ማንቀሳቀስ |
| 6. ማንከባለል | ረ. አመዛዝኖ ውሳኔ መስጠት |

ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለት

**በአካባቢያችሁ ካሉ ሰዎች ተረት ወይም አፈታሪክ ጠይቁ። ከዚያም ታሪኩን በማጥናት ተለማመዱትና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው።**

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

ተግባር ሦስት

## ቃለ መጠይቅ

**ለቀጣዮቹ መልሶች የሚመቹ ጥያቄዎችን አዘጋጁ።**

**(ጥያቄ 1 እንደ ምሳሌ ተሰርቷል)**

1. ጠያቂ፡ መልስሽን ተቀብለሻል?

   መላሽ፡ አዎ ተቀብያለሁ።

2. ጠያቂ፡______________________________

   መላሽ፡ ወደ አምቦ።

3. ጠያቂ፡______________________________

   መላሽ፡ ብርቱካን፣ ሙዝና ማንጎ።

4. ጠያቂ፡______________________________

   መላሽ፡ ሁል ጊዜ ስለማጠና።

5. ጠያቂ፡______________________________

   መላሽ፡ ባህላዊ ልብሶች።

6. ጠያቂ፡______________________________

   መላሽ፡ ከታናሽ እህቴ ጋር።

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

### ተግባር አራት

**ምን ብጠየቅ ደስ ይለኛል?**

**አንድ ሰው ወይም ጋዜጠኛ እናንተን አግኝቶ ጥያቄ መጠየቅ ቢፈልግ ስለምን እንዲጠይቃችሁ ትፈልጋላችሁ? መጠየቅ የምትፈልጓቸውን ጥያቄዎች በየግላችሁ ፃፉ:: ስትጨርሱም ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ጥያቄዎቹን በመለዋወጥ ተጠያየቁ።**

**ለምሳሌ፡** *እኔ መጠየቅ የምፈልገው፡-*

*መቼ እንደተወለድኩ፣ ስለአካባቢዬ፣ የት ትምህርት ቤት እንደተማርኩ፣ ወደፊት መሆን ስለምፈልገው ወዘተ*

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ተማሪዎች ተከታዩን ምንባብ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ተራ በተራ አንብቡ።**

# የተጠማችው ቁራ



በእለታት አንድ ቀን አንዲት የተጠማች ቁራ ውሃ ፍለጋ እየበረረች አካባቢዋን መቃኘት ጀመረች። ነገር ግን ምንም አይነት ውሃ ልታገኝ አልቻለችም። በዚህም **አቅሟ** ተዳከመ፤ ተስፋም ቆረጠች።



በድንገት ግን አንድ ማሰሮ ተመለከተች። ሆኖም የማሰሮው አንገት በጣም ጠባብ በመሆኑ ውሃውን ልትደረስበት አልቻለችም። ማሰሮውን **ዘቅዘቅ አድርጋም** ልትጠጣ ሞከረች። ማሰሮው ከባድ ስለነበር ይህም አልተሳካላትም።



ቁራዋ ለጥቂት ጊዜ በጥሞና አሰበች። በአካባቢዋ የድንጋይ ጠጠሮች ተመለከተች። ከዚያም ጠጠሮቹን እየለቀመች ማሰሮው ውስጥ ጨመረች። ጠጠሮቹ በርከት እያሉ ሲመጡ የውሃው ከፍታም ጨመረ። በመጨረሻም ቁራዋ ውሃውን እስኪበቃት መጠጣች!



ክፍለጊዜ፡ አስር

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

**በምንባቡ መሰረት 'እውነት' ወይም 'ሐሰት' በማለት በቃል መልሱ።**

1. ቁራዋ ስለራባት ምግብ ፍለጋ ብዙ ስትዞር ነበር።
2. ቁራዋ ማሰሮውን በክንፏ ይዛ ከፍ ብላ በረረች።

3. ቁራዋ ውሃውን ለመጠጣት ሦስት ጊዜ ሞክራለች።

4. ቁራዋ ተስፋ ብትቆርጥ ፍላጎቷ አይሳካም ነበር።

5. የማሰሮው አንገት በመስፋቱ ቁራዋ ውሃ ጠጣች።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ አምስት

**ሀ. ምንባቡን ደግማችሁ በማንበብ ለተከታዮቹ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

**ምሳሌ፡ ሞከረች ⟶ ጥረት አደረገች**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መቃኘት | በርከት | አቅሟ | እስኪበቃት | ዘቅዝቃ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

### መልመጃ ስድስት

**በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት መካከል ስም የሆኑትን ለዩ።**

**ምሳሌ፡- ድመት፣ ሀገር፣ ትህትና**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰማይ | አገኘች | ፈረስ | ተፃፈ | መሬት |
| እንደ | ዳቦ | ትህትና | ጠረጴዛ | ቆንጆ |
| ተቀመጠ | ኩራዝ | አረሰ | ጠጣ | ድመት |
| ሀገር | ብልጥ | ሶርሳ | እጅ | ገመቱ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

### ተግባር አምስት

የተጠማችው ቁራ ወደሚለው ምንባብ ተመለሱና በምንባቡ ውስጥ ስም የሆኑ ቃላትን ለዩ።

ለምሳሌ፡- ቁራ፣ ውሃ፣ አካባቢ ወዘተ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ሰባት

በሳጥኑ ውስጥ ከቀረቡት ቃላት እየመረጣችሁ አረፍተ ነገሮቹን አሟሉ።

**የቃላት ሳጥን**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዩኒቨርሲቲ | አናጢ | ጀግና | ለሲ |
| ትራክተር | ተጓዥ | መምህር | |

ምሳሌ፡

1. አውሮፕላን አብራሪ <u>ፓይሌት</u> ተብሎ ሲጠራ መርከብ ነጂ <u>መርከበኛ</u> ይባላል።
2. ሴት አሸናፊ <u>ጀግኒት</u> በሚል ስትታወቅ፣ ወንዱ ደግሞ ____________ይሰኛል።

3. እህቴ **ፈተናውን** ካለፈች በቀጣዩ አመት ________ ትገባለች።
4. ረዥም መንገድ የሚሄድ ሰው **መንገደኛ** ወይም __________ ይባላል።
5. የእንጨት ስራዎችን የሚሰራ ______ ሲባል ብረታ ብረትን የሚያቀልጥ **አንጥረኛ** ይባላል።
6. ባህላዊ እርሻ በ **በሬ** ሲካሄድ፣ ዘመናዊው እርሻ ደግሞ በ ___________ ይከናወናል።
7. የአገራችን የወንዶች የእግር ኳስ ቡድን **ዋልያ** ተብሎ ሲጠራ፣ የሴቶቹ ደግሞ _______ ይባላል።
8. ሴት አስተማሪ **መምህርት** ስትባል፣ ወንድ አስተማሪ ደግሞ _______ ይባላል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### ተግባር ስድስት

**በማዳመጥ ትምህርት ክፍል (አንበሳና ሰጎን) እና በማንበብ ትምህርት ክፍል (የተጠማችው ቁራ) የቀረቡላችሁ ምንባቦች ውስጥ ታሪኮቹ የያዟቸውን ዋና ዋና ሀሳቦች ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡ።**

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

*ስም የሰዎች፣ የቦታዎች ወይም የነገሮች መጠሪያ ወይም ስያሜ ነው።*

**ምሳሌ:-** *ሶለኔ፣ አወዳይ፣ መኪና፣ ወንዝ*

### መልመጃ ስምንት

**በክፍላችሁ ያሉ ነገሮች መጠሪያዎችን ፃፉ።**

**ምሳሌ፡** ሰሌዳ፣ ጣሪያ፣ ወንበር

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ ዘጠኝ

**የሚከተሉት አረፍተነገሮች ደብተራችሁ ላይ ፃፉና ስሞች የሆኑትን ቃላት አስምሩባቸው።**

ምሳሌ:- <u>ኢያቴ ተረት</u> ነገረችኝ። *(ኢያቴ እና ተረት)*

1. ሶፊያ መፅሐፍ አዋሰችኝ።
2. ዝናብ እየዘነበ ነው።
3. ዛፉ ላይ ወፎች ጎጆ ሰርተዋል።
4. መንገሻ ወደ ቡሌ ሆራ ሄደ።
5. እንቆቅልሽ የሚጠይቀኝ እፈልጋለሁ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### ተግባር ሰባት

**ቀጥለው የቀረቡላችሁን ፊደላት በመጠቀም ስም የሆኑ ቃላትን መስርቱ።**

**ምሳሌ፡- ተማሪ፣ እህት**

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ | መ | ፍ | ን | ም | እ | ት | ማ | በ | ር | ረ |
| ዝ | ቀ | ከ | ጠ | ሐ | ሙ | ክ | ፍ | ል | ሪ | ፅ |
| ወ | ድ | ህ | ገ | ስ | ለ | ሰ | ፍ | ው | | |

# ምዕራፍ አራት፡ የጊዜ አጠቃቀም

ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል 'ጊዜዬን ባግባቡ እጠቀማለሁ እናንተስ' የሚል ፅሑፍ እና የተለያዩ መልመጃዎችና ተግባራት ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሩ።**

## የጊዜ አጠቃቀም

1. በየቀኑ ምን ምን ተግባራትን እንደምታከናውኑ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ?
2. ወደ ትምህርት ቤት የምትሄዱት ስንት ሰዓት ነው?

**መምህር የሚያቀርቡላችሁን ገለፃ አዳምጡ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3፡00 | 4፡15 | 5፡30 | 6፡05 | 7፡20 |
| 9፡35 | 10፡40 | 10፡45 | 11፡50 | 12፡55 |

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከመኝታችሁ ስንት ሰዓት ነው የምትነሱት?
2. ትምህርት ቤት ስንት ሰዓት ትደርሳላችሁ?
3. ምሳችሁን ስንት ሰዓት ነው የምትበሉት?

**መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ምንባብ በጥሞና አዳምጡ።**

## ጊዜዬን በአግባቡ እጠቀማለሁ፤ እናንተስ?







## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

ባለፈው ክፍለ ጊዜ ያዳመጣችሁት ምንባብ ተደግሞ ሲነበብ አዳምጡ።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ።**

1. ባለታሪኳ በጥዋት ተነስታ፣ __________ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለች።
2. ባለ ታሪኳ የህዝብ መዝሙር የምትዘምረው ከማን ጋር ነው?
3. ባለታሪኳ ከእረፍት ሰዓት በኋላ ወዴት ትሄዳለች?
4. ከጓደኞቿ ጋር ስለምን ተመካከሩ?

### መልመጃ ሁለት

**ቃላቱን ከተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እጫወታለሁ | ሀ. ጎበዝ |
| 2. አመራለሁ | ለ. እዝናናለሁ |
| 3. ሲጠናቀቅ | ሐ. ተነጋገርን |
| 4. ተፎካካሪ | መ. እሄዳለሁ |
| 5. ተመካከርን | ሠ. ሲያልቅ |

## ክፍለጊዜ፡ አራት







## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ሰዓት አጠያየቅና አመላለስ

*ተማሪዎች ሰዓት በምንጠይቅበትና በምንመልስበት ጊዜ በአክብሮትና በትህትና መሆን ይገባዋል። ሰዓት ስንጠይቅ አስቀድመን ሰላምታ ማቅረብና 'እባክህ፣ እባክሽ፣ እባክዎ' የሚሉ ትህትና አዘል አገላለፆችን መጠቀም ይኖርብናል። በሌላ በኩል ሰዓት ስንጠየቅ፣ 'እሺ፣ ችግር የለውም፣ በትክክል' የሚሉ አገላለፆችን እንጠቀማለን።*

| ሙሉ ሰዓት ሲሆን | ከአምስት/ከአስር/ከሃያ/ ከሃያ አምስት | ከሩብ/ ተኩል | እሩብ/ሃያ/ ሃያ አምስት ጉዳይ |
|---|---|---|---|
| 6፡00 | 6፡05፣ 6፡10፣ 6፡20... | 6፡15፣ 6፡30 | 6፡45፣ 6፡40 |

ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር አንድ




በስዕል የቀረቡት ሰዓት አመልካቾች የሚያመለክቱን ሰዓትና ደቂቃ እየተመለከታችሁ አቆጣጠሩን ከጓደኞቻችሁ ጋር ተለማመዱ።

ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ተግባር ሁለት

ወላጆቻችሁን ወይም ሌሎች ሰዎችን የቀናትና የወራትን ስሞች ጠይቁ። ይህንን በተመለከተም ለክፍል የቃል ዘገባ አቅርቡ።

1. ከሰኞ እስከ እሁድ ያሉ ቀናት እነማን ናቸው?

2. አስራ ሦስቱን ወራት አጥንታችሁ አቅርቡ።

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

**ተግባር ሦስት**

**በአንድ ቀን ውሏችሁ ምን ምን ተግባራትን እንደምታከናውኑ (ትምህርት ቤትና ቤታችሁ) ተራ በተራ እያነሳችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩ።**

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

**ተግባር አራት**

**ጊዜን በአግባቡ መጠቀም የሚኖረውን ፋይዳ በተመለከተ መረጃ አሰባስቡ። ጊዜያቸውን በአግባቡ በመጠቀማቸው ውጤታማ የሆኑ የአካባቢያችሁን ሰዎች በምሳሌነት በመጥቀስም ስለልምዳቸው ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ።**

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ተግባር አምስት**

**ቀጣዩን ምልልስ ጥንድ ጥንድ በመሆን አስቀድማችሁ በመለማመድ ክፍል ውስጥ በንባብ አቅርቡት።**

**መንገደኛ፡** እንደምን አደሩ እመቤት?

**ወ/ሮ ማንጠግቦሽ፡** ይመስገነው እኔ ደህና ነኝ። አንተ
እንዴት ነህ?

**መንገደኛ፡** ደህና ነኝ፣ ፈጣሪ ይመስገን። ሰዓት
ልጠይቀዎት ብዬ ነው።

**ወ/ሮ ማንጠግቦሽ፡** እስቲ ልይልህ…አዎ… ከሩብ ነው።
(ሰዓት እጃቸው ላይ እያዩ)

**መንገደኛ፡** ስንት ከሩብ?

**ወ/ሮ ማንጠግቦሽ፡** አምስት ከሩብ።

**መንገደኛ፡** አመሰግናለሁ። ስድስት ከሰላሳ ላይ ቀጠሮ
አለብኝ፤ እደርሳለሁ። በሉ ደህና ሁኑ።

**ወ/ሮ ማንጠግቦሽ፡** ስድስት ተኩል ማለትህ ነው?
**መንገደኛ፡** አዎ ስድስት ተኩል ማለቴ ነው።

**ወ/ሮ ማንጠግቦሽ፡** መልካም፤ በል ደህና ሁን ልጄ።
ሁሌም ቀጠሮ ማክበር ጥሩ ነው።

**መንገደኛ፡** አዎ እማማ፤ ቀጠሮ ማክበር የስልጣኔ ምልክት
ነው።

**ወ/ሮ ማንጠግቦሽ፡** ጎሽ እንደዚያ ነው፤ የሚባለው። ጊዜ
ያከበሩትን ያከብራል። ደህና ዋልልኝ።

**መንገደኛ፡** አሜን እርስዎም ደህና ይዋሉልኝ!

## ክፍለጊዜ፡ አስር

### መልመጃ ሦስት

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

1. መንገደኛው ወይዘሮ ማንጠግቦሽን እንዴት ነበር ያናገራቸው?
2. መንገደኛው ወይዘሮ ማንጠግቦሽን የጠየቃቸው ምን ነበር?
3. ‘ስድስት ከሰላሳ’ ሲል ምን ማለቱ ነበር?
4. “ቀጠሮ ማክበር የስልጣኔ ምልክት ነው” ያለው ማነው?
5. “ጊዜ ያከበሩትን ያከብራል።” የሚለው አባባል ምን ማለት ነው?
6. እናንተ ቀጠሮ ታከብራላችሁ? ቀጠሮ ማክበር ያለውን ጠቀሜታ አስረዱ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

**በዚህ ክፍል የቃላት ትምህርት ቀርቦላችኋል። ትዕዛዛቱን ተከትላችሁ ስሩ።**

## የተውሶ ቃላት

ስለውሰት መምህር የሚሰጧችሁን ገለፃ አዳምጡ።

### መልመጃ አራት

በ'ሀ' ስር የተጠቀሱትን የተውሶ ቃላት በ'ለ' ስር ካሉ አማራጮቻቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሞባይል | ሀ. መልዕክት |
| 2. ቴሌቪዥን | ለ. ያልተሳካ ጥሪ |
| 3. ሜሴጅ | ሐ. ትንግርተ ሳጥን |
| 4. ሚስ ኮል | መ. በይነ መረብ |
| 5. ኢንተርኔት | ሠ. የእጅ ስልክ |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

በዚህ ክፍል መፃፍን ለማለማመድ የሚያስችሉ መልመጃዎችና ተግባራት ቀርበዋል:: በመመሪያዎቹ መሰረት ስሩ።

### መልመጃ አምስት

በአሃዝ የተሰጡትን በፊደል ቀይራችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፡

2፡ 15 → ሁለት ከሩብ

4፡ 20 → አራት ከሃያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3፡25 | 6፡00 | 7፡30 | 8፡45 |
| 9፡05 | 10፡35 | 11፡20 | 2፡00 |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

### ተግባር ስድስት

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አረፍተነገሮች ፃፉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### ተግባር ሰባት

በቤትና በትምህርት ቤት የምታከናውኗቸውን ተግባራት ተከታዩን ሰንጠረዥ በመጠቀም አሟሉ።

| ስፍራ | የሚከናወኑ ተግባራት | ማከናወኛ ጊዜ |
|---|---|---|
| ቤት ውስጥ | | |
| ትምህርት ቤት | | |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

### መልመጃ ስድስት

ቀጥሎ በቀረበው ሳጥን ውስጥ ካሉ ቃላት ግስ የሆኑትን ለይታችሁ አመልክቱ።

**ምሳሌ፡-** መጣ፣ ለገሰ፣ አቀበለ…

| | | | |
|---|---|---|---|
| መቁጠሪያ | ጊዜ | ነበር | ገመተ |
| ተናገረ | ብልህ | አጎረሰ | ቀልድ |
| ጠጣ | ጻፈ | ተፈተነ | አስመጣ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ሰባት

**ሀ. ተከታዮቹን ግሶች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ተጠቀመች | ደረሱ | ፃፍኩ | አገኘን |
| አሸነፋችሁ | ወሰደ | ሄደች | ተጠቀመ |

ግስ በአረፍተ ነገር ውስጥ በማሰሪያ አንቀፅነት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡ *ግስ* → አካፈለ፣ አመጣች

*ማሰሪያ አንቀፅ*

ሀ. የያዘውን ብርቱካን ለጓደኞቹ **አካፈለ**።

ለ. አዲስ የገዛችውን መፅሐፍ **አመጣች**።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ ስምንት

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ፃፏቸውና ግስ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ አስምሩባቸው።**

1. አሚናና ሲፈን ወደ ገበያ ሄዱ።
2. ለእህቱ ደብዳቤ ፃፈና ላከላት።
3. ሌባው በፖሊስ ተያዘ።
4. ጊዜዬን ለአልባሌ ተግባር አላውልም።
5. አዲስ ደብተር ዛሬ ተገዛልኝ።
6. አባቴ ሰባት ሰዓት ላይ ዜና ያዳምጣል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### መልመጃ ዘጠኝ

**ማሰሪያ አንቀጾችን በመጠቀም ባዶ ቦታውን አሟሉ።**

1. እኔና እህቴ ወደ አያታችን ቤት ________።
2. መምህራችን ሲያስተምሩ ማስታወሻ _______።
3. ጊዜያችንን በአግባቡ __________።
4. ታላላቆቻችንን እናከብር ወላጆቻችንን ______።
5. ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ጠንክሬ ________።

6. ገመቺስ ብርቱካን ________፡፡
7. ሐለን ወደ ከአሶሳ ________፡፡
8. ከፍተኛ ዝናብ በመዝነቡ ወንዙ _______፡፡
9. ህፃናት ፍቅርና እንክብካቤ _________፡፡
10. የህዳሴ ግድቡ ኤሌክትሪክ _________፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡ መጓጓዣ




## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**ይህ ትምህርት ክፍል የማዳመጥ ክሂላችሁን የምታሻሽሉበት ነው። 'መጓጓዣ' በሚል ርዕስ መምህራችሁ ምንባብ ያነቡላችኋል:: ተግባርና መልመጃዎቹን ትዕዛዙን በመከተል ስሩ።**

## መጓጓዣ

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ወደ ትምህርት ቤት የምትመጡት በምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ ሰዎች ከቦታ ቦታ በምን አይነት መጓጓዣ ይንቀሳቀሳሉ?

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

### ሀ. ያዳመጣችሁትን መሰረት በማድረግ መልሱ።

1. ምንባቡ የሚነግረን ስለምንድን ነው?
2. የመጓጓዣ አይነቶች ስንት ናቸው? ስማቸውስ?
3. ለተጠቀሱት የመጓጓዣ አይነቶች ምሳሌ ስጡ።
4. ዘመናዊ መጓጓዣዎች ከባህላዊዎቹ በምን ይለያሉ?

**ክፍለጊዜ፡ ሁለት**

### ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሑፍ መልሱ።

1. ባህላዊዎቹ መጓጓዣዎች ከዘመናዊዎቹ ተመራጭ የሚሆኑበት በምን ምክንያት ነው?
2. ዘመናዊዎቹ መጓጓዣዎች ከባህላዊዎቹ በምን ይለያሉ? የሚለዩባቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ።
3. የትኛውን የመጓጓዣ አይነት መጠቀም እንደምትፈልጉ በምክንያት አስደግፋችሁ አስረዱ።
4. ‘መጓጓዣ’ የሚለውን እየተካው የመጣው ቃል የቱ እንደሆነ ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### ተግባር አንድ

**ሰዎች በአካባቢያችሁ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀሟቸውን መጓጓዣዎች በተመለከተ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ። አንድ ተማሪ ሲናገር ሌሎቻችሁ በተራችሁ አዳምጡ።**

**የምታነሷቸው ነጥቦች፡-**

- አይነቶቹን
- ምሳሌዎች የሚሆኑ
- ምን ጥቅምና ጉዳት እንዳላቸው
- ብዙ ሰዎች የትኞቹን እንደሚጠቀሙ ወዘተ

## ክፍለጊዜ፡ አራት

### መልመጃ ሁለት

**ለሚከተሉት ቃላት በተደመጠው ምንባብ መሰረት ፍቺ ስጧቸው። ቀጥሎም በቃል አረፍተ ነገር መስርቱባቸው።**

**ምሳሌ፡-** ተደራሽ → ሁሉም ቦታ የሚገኝ

ባህላዊ መጓጓዣ ለሁሉም ተደራሽ ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ውድ | ዘገምተኛ | ዘመናዊ |
| የሚከናወን | ባህላዊ | ምቾት |

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለት

**ስለባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ አጭር ንግግር ተራ በተራ አድርጉ። ንግግራችሁን ስታቀርቡ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት አስገቡ።**

- ስለመጓጓዣ አይነቶቹ ምንነት፣
- ጥቅምና ጉዳታቸው
- ምሳሌ የሚሆኑ (ለዘመናዊም ለባህላዊም) ፣
- ምሳሌ የማይሆኑ (ለምሳሌ በቅሎ ለዘመናዊ፣ ባቡር ለባህላዊ ማጓጓዣ አይነት ምሳሌ አይሆኑም)

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

### ተግባር ሦስት

**ተማሪዎች አምስት ወይም ስድስት አባላት ያለው ቡድን መስርቱ። ክብ ስሩና በምሳሌው መሰረት በዜማ ጥያቄ ተጠያየቁ። ተጠያቂ መሃል ይሆናል።**

| ጥያቄ (የቡድኑ አባላት አንድ ላይ) | መልስ (ተጠያቂ) |
|---|---|
| እንዴት ነሽ/ህ? | ደህና ነኝ። |
| ስምሽ/ህ ማነው? | ኪያ ግርማ። |
| የት ትኖሪያለሽ/ትኖራለህ? | ቡሌ ሆራ። |
| ምን መመገብ ትወጃለሽ/ትወዳለህ? | ዳቦ በወተት። |
| የት ትማሪያለሽ/ትማራለህ? | ሆራ ቁጥር 1። |
| ትምህርት ቤት በምን ትሄጃለሽ /ትሄዳለህ? | በታክሲ። |
| በትምህርትሽ/ህ እንዴት ነሽ/ህ? | ጎበዝ ነኝ። |
| ወደፊት ምን መሆን ትፈልጊያለሽ /ትፈልጋለህ? | መድሃኒት ቀማሚ |
| ቻዎ ቻዎ! | ቻዎ ቻዎ! |

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ



# የበረሃው መርከብ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የቀጣዩን ምንባብ አንቀፆች ተከፋፍላችሁ ተራ በተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ።**

1. በአካባቢያችሁ ለመጓጓዣነት የሚያገለግሉ እንስሳትን ስም ጥቀሱ?
2. ከዚህ በፊት ግመል አይታችሁ ታውቃላችሁ?

ግመል 'የበረሃው መርከብ' የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ምክንያቱም በረሃማ አካባቢዎች ለሚኖሩ ሰዎች ዋነኛ መጓጓዣ በመሆኑ ነው። ግመል በአገራችን በብዛት በሶማሌና አፋር አካባቢዎች ይገኛል። ግመል ውሃ አንዴ ከጠጣ ለረጅም ጊዜ ያለውሃ መቆየት ይችላል። ይህም በበረሃማ ሥፍራ እንዲኖር አስችሎታል።

ግመል የሰው ልጆች ካለመዷቸውና ቅርባቸው ካደረጓቸው እንስሳትም አንዱ ነው። የሰው ልጆች ግመልን ከመጓጓዣነት ባለፈ ስጋውንና ወተቱን ለምግብነት፣ ቆዳውን ለተለያየ አላማ ይጠቀሙበታል። ግመል ሳር በል ከሆኑት እንስሳት ተርታ ይመደባል፤ ስለሆነም ቅጠላቅጠል፣ ፍራፍሬዎቸንና ስራስሮችን ይመገባል።

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሦስት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች 'እውነት' ወይም 'ሐሰት' በማለት በቃል መልሱ።**

1. ግመል የሚታወቀው ደጋማ በሆኑ አካባቢዎች በመኖር ነው።
2. ግመል የሚመገበው ቅጠላቅጠል፣ ፍራፍሬና ስራስሮችን ነው።
3. ከመጓጓዣነት በተጨማሪ ግመል ለምግብነትም ይውላል።
4. ግመል የሰው ልጆች ካለመዷቸው እንስሳት ብቸኛው ነው።

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

### መልመጃ አራት

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በፅሑፍ መልሱ።**

1. የበረሃው መርከብ የተባለው ማን ነው?
2. ግመል በበረሃማ ስፍራ መቆየት እንዴት ቻለ?
3. ግመል በየትኞቹ እንስሳት ምድብ ይካተታል?
4. ከመጓጓዣነት ባለፈ ሰዎች ግመልን ለምን ተግባር ይገለገሉበታል?

ክፍለጊዜ፡ አስር

# የእረፍት ቀን ጉብኝቴ

## የቅድመንባብ ጥያቄዎች

**የነዚህን ቃላት ፍቺ ገምቱ**

ተፈናጠጥኩ ስንጓዝ እያወዛወዙ ይማርካል

1. በእረፍት ቀናችሁ የት ታሳልፋላችሁ?
2. ዘመዶቻችሁን ለመጎብኘት በቅርቡ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? (ጊዜውና ቦታውን ተናገሩ)

ከእለታት አንዱ ቀን እኔ፣ እህቴና ወላጆቼ በገጠር ያሉ ዘመዶቻችንን ለመጎብኘት ተነሳን። እናቴ ጉዟችን ሁለት ሰዓት ያህል እንደሚፈጅ ነገረችኝ። የምንሄደውም በፈረስ እንደሆነ አስረዳችኝ።



በሚቀጥለው ቀን ጉዞው ተጀመረ። እኔ ከናቴ ጋር ፈረሱን ተፈናጠጥኩ። እህቴ ደግሞ ከአባቴ ጋር በሌላ ፈረስ ተፈናጠጠች። ለመጀመሪያ ጊዜ በፈረስ መጓዝ በጣም ያስፈራል። ከኋላ ስለነበርኩና ስለፈራሁ እናቴን ወገቧን ጥብቅ አድርጌ ያዝኳት። ጥቂት ስንጓዝ ግን ፍርሃቱ እየለቀቀኝ ሄደ። ዘና ብዬ መሄድ ጀመርኩ። እህቴ እንደኔ የፈራች አትመስልም።

በመንገዳችን ላይም ብዙ አስደሳች ነገሮችን አየን። የተለያዩ እፅዋት፣ ትላልቅ ዛፎችና ቁጥቋጦዎች በየአይነታቸው አሉ። ጦጣ፣ ጉሬዛና ዝንጀሮዎች እኛን ሲያዩ ከዛፍ ዛፍ ይዘሉ ነበር። ሚዳቋዎች ጆሯቸውን ቀጥ አድርገውና ጅራታቸውን እያወዛወዙ በተጠንቀቅ ሳር ይነጫሉ። የአዕዋፍቱ አይነት፣ ብዛትና ዝማሬ ቀልብን ይማርካል። እነዚህን እያየን ያለድካም የጉዟችን መዳረሻ ደረስን። ሲጠብቁን የነበሩት ዘመዶቻችን በደስታ እያቀፉና እየሳሙ ተቀበሉን።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አምስት

**ቀጣዮቹን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ።**

1. ለመጓጓዣነት የዋለው እንስሳ ማን ነበር?
2. በጉዞው ላይ ስንት የቤተሰብ አባላት ተሳትፈዋል?
3. የተጓዦቹ የጉዞ አላማ ምን ነበር?
4. ተራኪው የተፈናጠጠው ከማን ጋር ነበር?
5. ተራኪዋ የፈራችው በምን የተነሳ ነው?

ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ ስድስት

**የእረፍት ቀን ጉብኝቴ በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ፅሑፍ መልሳችሁ በማየት ለእነዚህ ቃላት አገባቢያዊ ፍቺ ስጡ። ምላሾቻችሁንም እያነፃፀራችሁ ተነጋገሩ።**

| | | |
|---|---|---|
| ለመጎብኘት | እንደሚፈጅ | ቀልብን |
| ተፈናጠጥኩ | መዳረሻ | እየለቀቀኝ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

### መልመጃ ሰባት

በምስል የተገለፁትን የመጓጓዣ አይነቶች ከስያሜዎቻቸው ጋር አዛምዱ።

| | ሀ | ለ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ሞተር ሳይክል | ሀ |  |
| 2 | በቅሎ | ለ |  |
| 3 | ሚኒባስ | ሐ |  |
| 4 | የጭነት መኪና | መ |  |
| 5 | ጋሪ | ሠ |  |
| 6 | ባጃጅ | ረ |  |
| 7 | ታንኳ | ሰ |  |
| 8 | ፈጣን ባቡር | ሸ |  |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

### መልመጃ ስምንት

**በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመምረጥ አረፍተነገሮቹን አሟሉ።**

| ዘመድ | ተሽርካሪዎች | እንድከላከል | ልምድ | ጫወታ | ፎቆች |
|---|---|---|---|---|---|

1. የሰለሞን እናት በእግር የመጓዝ ______ አላቸው።
2. ሰማይ ጠቀስ _______ በአገራችን እየተገነቡ ነው።
3. መከተቤ እራሴን ከበሽታ ________ ረድቶኛል።
4. ሴናፍ በእረፍት ቀኗ ________ ትጠይቃለች።
5. የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡ _____ እዚህ አሉ።
6. _______ መንፈስን ያድሳል፤ ደስተኛም ያደርጋል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ዘጠኝ

**ቀጥለው መጓጓዣ የሆኑ ነገሮችን የሚወክሉ ቃላት ቀርበዋል። ተገቢ ሆሄያትን ጨምራችሁ አሟሏቸው።**

**ምሳሌ፡** መ__ና ⟶ መኪና

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አ__ሮፕላን | መ. ጋ__ | ሰ. አው__ቢስ |
| ለ. __ረስ | ሠ. መር__ብ | ሸ. ጀ__ባ |
| ሐ. ባቡ__ | ረ. __ስክሌት | ቀ. ሠረ__ላ |

## መልመጃ አስር

ከላይ ያሚላችኋቸውን የመጓጓዣ አይነቶች የየብስ(የመሬት)፣ የውሃና የአየር ብላችሁ መድቧቸው።

| የየብስ | የውሃ | የአየር |
|---|---|---|
| መኪና | - | - |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት**

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

## መልመጃ አስራ አንድ

**ሀ. በቀጣዮቹ አረፍተነገሮች ውስጥ ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀ ቃላትን አስተካክላችሁ ጻፉ።**

1. ተገዛልኝ ሹራብ ቀይ።
2. እህቴ በጊዜ ትሰራለች የቤት ስራዋን።
3. ትራንስፖርት አይነት ነው አውሮፕላን የአየር።
4. ሄደች ገበያ ወደ በባጃጅ እናቴ።
5. የሚበላ ፍራ ፍሬ ልጅ ነው ጤናማ።

**ለ. የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ።**

1. ለእርሻ የተዘጋጀው መሬት ታረሰ።
2. ሌላው ደግሞ ገበያ ወጥቶ ተሸጠ።
3. የጤፉ ምርጥ ዘር ተዘራበት።

4. ቆይቶም አረም እንዳያጠቃው ታረመ።
5. የተወሰነው ለምግብነት ዋለ።
6. የታጨደው ተወቅቶ ወደ ጎተራ ገባ።
7. ጤፉ ለአጨዳ ደረሰ ታጨደ።
8. ከሳምንታት በኋላ ዘሩ መብቀል ጀመረ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

## ቅጽሎች

- **ቅፅሎች** ከስም በፊት እየገቡ ስምን የሚገልፁ ናቸው።
- **ቅፅሎች** የሚገልፁት የስምን መልክ፣ መጠን፣ ሁኔታ ወዘተ ነው።

**ምሳሌ፡** ሀ. **ሰፊ** መንገድ ለ. **ትንሽ** ብስክሌት
ሐ. **አሮጌ** መኪና

## መልመጃ አስራ ሁለት

1. ቅፅሎችን ተጠቀማችሁ በአካባቢያችሁ ያሉ ነገሮችን ግለፁ::

   ሀ. ጥቁር በቅሎ ለ. ብዙ መኪናዎች

2. በምሳሌው መሠረት ቅፅሎችና ስሞች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

**ምሳሌ፡** ሀ. በአካባቢያችን ሰፊ መንገድ ተገንብቷል።

ለ. እኛ ጥቁር በሬ አለን።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስራ ሦስት

**በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ቅፅሎችን ለይታችሁ አመልክቱ።**

**ምሳሌ፡** ቤተሰቦቼ ሰፊ እርሻ አላቸው። (ሰፊ)

1. ሰብስቤ አሮጌ መኪና ገዛ።
2. ቦንቱ ነጭ ቀሚስ ለብሳለች።
3. ጎበዝ ተማሪዎች ሁልጊዜ ይሸለማሉ።
4. ዘመናዊ መጓጓዣዎች ጊዜ ቆጣቢ ናቸው።
5. አበበች ሰማያዊ ቦርሳ አንጠልጥላለች።
6. መምህራችን ትልቅ መፅሐፍ ይዘዋል።
7. ረጅሙ ድልድይ ተገንብቶ አለቀ።
8. ሙስጠፋ አዲስ ቤት እያሰራ ነው።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### መልመጃ አስራ አራት

**ዘመናዊና ባህላዊ መጓጓዣዎችን በተመለከተ አጫጭር አረፍተነገሮች ፃፉ።**

**ምሳሌ፡** 1. በቅሎ ዕቃ ለማጓጓዝ ታገለግላለች።

2. መርከብ በውሃ ላይ ይጓዛል።

# ምዕራፍ ስድስት፡ ስነምግባር

ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል ‘ቲቶ’ በሚል ርዕስ ምንባብ ይነበብላችኋል:: ምንባቡን አዳምጣችሁ ተግባራትና መልመጃዎቹን ትሰራላችሁ።

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ምን አጥፍታችሁ ተመክራችሁ ታውቃላችሁ?
2. ከዚህ ቀደም ይቅርታ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ?

ክፍለጊዜ፡ ሁለት

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

#### መልመጃ አንድ

ሀ. ተማሪዎች መምህራችሁ ያነበቡላችሁን ምንባብ ዋና ዋና ነጥቦች መልሳችሁ ተናገሩ።

ለ. ባዶ ቦታዎቹን በተደመጠው ምንባብ መሰረት ሙሉ።

1. ቲቶ በጥፋቱ ____________ እንዲጠራ ተደረገ።

2. መምህርቷና የቲቶ ወላጆች ቲቶ በሚያሳየው ያልተገባ ባህሪ ዙሪያ ___________::
3. ቲቶ ______ ብሎ ለአለልቱ እርሳሷን መለሰላት።
4. በመጨረሻም ቲቶ ተወዳጅ፣ ለወላጆቹ ________፣ ሰው አክባሪና እና ከጓደኞቹ ጋር በ ________ የሚጫወት ሆነ።

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

## መልመጃ ሁለት

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በፅሑፍ መልሱ።**

1. ቲቶ ተውሶ ያልመለሰው የማንን እርሳስ ነበር?
2. የምንባቡ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?
3. ቲቶ ያደረጋቸውን ያልተገቡ ተግባራት ዘርዝሩ።
4. የቲቶ መምህርት ምን አደረገች?
5. ቲቶ ጥፋቱን አምኖ ምን አደረገ?
6. በመጨረሻ ቲቶ ምን አይነት ልጅ ሆነ?

## ክፍለጊዜ፡ አራት

### መልመጃ ሦስት

በተደመጠው ታሪክ መሰረት በ 'ሀ' ስር ለቀረቡት ቃላት ፍቻቸውን ከ'ለ' ስር በመፈለግ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አለመታዘዝ | ሀ. መነጋገር |
| 2. ማርፈድ | ለ. ምሳሌ መሆን |
| 3. መዋስ | ሐ. ክፉ ማድረግ |
| 4. ተንኮል | መ. እሺ ብሎ መቀበል |
| 5. መወያየት | ሠ. ለመመለስ መውሰድ |
| 6. ማመን | ረ. የሚታይ ባህሪ |
| 7. አርዓያ | ሰ. እንቢ ማለት |
| 8. ስነምግባር | ሸ. በጊዜ አለመድረስ |


## ክፍለጊዜ፡ አምስት


## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

ቀጣዮቹን ስዕሎች አጥኗቸውና ጥሩና መጥፎ ስነምግባሮችን ለዩ። የለያችኋቸው የትኞቹ እንደሆኑም በምክንያት አስደግፋችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።






## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ተግባር ሁለት

**ከተከታዮቹ ነጥቦች በመነሻነት እየመረጣችሁ ጥሩ ስነምግባር የተላበሰ ሰው ምን እንደሚያደርግ ተናገሩ።**

**ነጥቦች፡-**

- ንፅሕና መጠበቅን በተመለከተ
- ከአለባበስ ጋር በተያያዘ
- ታላላቆችን ማክበርን በተመለከተ
- ጊዜ አጠቃቀምን አስመልክቶ
- የሌሎች ሀሳብን ስለማክበር

- ጓደኞችን መውደድን በተመለከተ
- ለወላጆች መታዘዝን አስመልክቶ
- አካባቢን ስለመንከባከብ
- አገርን ከመውደድ ጋር በተያያዘ

**ምሳሌ፡-** *በእኔ አመለካከት ጥሩ ስነምግባር የተላበሰ ሰው ንፅህናውን ይጠብቃል።*

- *ለእኔ ጥሩ ስነምግባር የተላበሰ ሰው ጊዜን በአግባቡ የሚጠቀም ነው*

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

**ተግባር ሦስት**

**በአነስተኛ ቡድን በመደራጀት ጥሩ ወይም መጥፎ ስነምግባር ስላላቸው ሰዎች ተወያዩ።**

**ክፍለጊዜ፡ ስምንት**

## መዝሙር

**መምህራችሁ የሚያስጠናችሁን ዜማ በመከተል ቀጣዩን ግጥም ተለማምዳችሁ ክፍል ውስጥ ዘምሩ።**

እኔ እኔ …እኔ እኔ

*(በጣት ወደ ራስ በመጠቆም)*

የጥሩ ስነምግባር ባለቤት ነኝ

ጓደኞቼ፣ ሰው ሁሉ የሚወደኝ።

ታላላቅን አከብራለሁ

ወላጆቼን እታዘዛለሁ

እኔ እኔ ...እኔ እኔ

ትምህርት ቤት አላረፍድም

(*ጠቋሚ ጣት ግራ ቀኝ ማወዛወዝ*)

ከማንም ጋር አልጣላም

እኔ እኔ ... እኔ እኔ

ይቅርታ ማለት ልማዴ ነው

ውሸት፣ ስርቆት እእ እእ

(*አንገትና ጠቋሚ ጣት በማወዛወዝ*)

ሰው ማስቀየም እእ እእ

እኔ እኔ ... እኔ እኔ

ሀገሬንም እወዳለሁ

(*እጅ በደረት*)

ለወገኔ እቆማለሁ

ተምሮ ማወቅ ፈልጋለሁ

(*የማንበብ ምልክት፣ እጅ ተከፍቶ፣ አንገት ዝቅ*)

ሰርቶ ለማደግ እጥራለሁ

(*እጅ ተጨብጦ የመሮጥ አይነት እንቅስቃሴ*)

ህልሜን ሁሉ አሳካለሁ

እኔ እኔ … እኔ እኔ

እርግጠኛ እርግጠኛ! (ጭብጨባ)

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

**ቀጣዩን ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ።**



## ውሸታሟ ጦጣ

1. ስለ ጦጣ የተነገረ የምታውቁት ተረት አለ?
2. የነዚህን ቃላት ፍቺ ገምቱ


/ወጥመድ፣ ባህላዊ፣ መቆራመት/

ከእለታት አንድ ቀን አንዲት ጦጣ ቤተሰቦቿን "ነብር መጣ…ነብር መጣ!" እያለች አሯሯጠቻቸው። እየሳቀችም "ውሸቴን እኮ ነው!" አለቻቸው። በሌላ ጊዜም "ሩጡ ሩጡ! ነብር ነብር!" እያለች ጮኸች። ወላጆቿም

እውነት መስሏቸው ሮጠው ዛፍ ላይ ወጡ። ወደ መሬት ሲመለከቱም እንድም ነገር የለም። ውሸታም ልጅ ስላላቸውም አዘኑ።

*1. ጦጣዋ ቤተሰቦቿን ____________________ ።*

*2. የጦጣዋ ወላጆች ሮጠው _____________ ላይ ወጡ።*



ከቀናት በኋላም ውሸታሟ ጦጣና ቤተሰቧ ምግብ ፍለጋ ወጡ። እሷም ከኋላ ኋላ ትሄድ ነበር። ተደብቃ በሌላ መንገድ ስትሄድም አንድ እግሯ በወጥመድ ተያዘ። “እባካችሁ አድኑኝ ወጥመድ ያዘኝ!” እያለች ጮኸች። ቤተሰቦቿ ግን እንደለመደችው ልትዋሸን ነው ብለው፤ ምግብ ፍለጋቸውን ቀጠሉ። “ውሸታምነቴ ነው ለዚህ ያበቃኝ በቃ መሞቴ ነው” እያለች አለቀሰች።

*3. ጦጣዋን የያዛት ____________ ነው።*

*4. ልጆች ጦጣዋ ምን የምትሆን ይመስላችኋል?*



ቆይቶም ወላጆቿ ዞር ብለው ሲያዩ ውሸታሟ ጦጣ የለችም። "አንቺ ውሸታም አውቀንብሻል ነይ ውጪ!" ብለው ቢጣሩም መልስ አላገኙም። "ወይኔ ልጃችን" እያሉም ቅድም ወደ ጮኸችበት አካባቢ ተመለሱ። ወጥመዱ እግሯን ይዟት በሐዘን ተቆራምታ አገኟት። ቀስ ብለውም የቆሰለ እግሯን አላቀቁላት። ከወጥመዱ እንደወጣችም "እባካችሁ ወላጆቹ ይቅርታ አድርጉልኝ፤ ሁለተኛ ውሸት የሚባል ነገር አልናገርም" አለች። እነሱም ይቅርታ አድርገንልሻል ብለው ቁስሏን በባህላዊ መድሃኒት አሸጉላት። ከዚህ ጊዜ በኋላም ውሸት መናገር አቆመች።

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

**ሀ. ተከታዮቹን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

1. የውሸታሟን ጦጣ ታሪክ በቃላችሁ ተናገሩ።

2. ልጆች ከጠጣዋ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

3. የጠጣዋ ወላጆች ያዘኑት ለምንድን ነው?

4. የሚዋሽ ሰው ምን የሚደርስበት ይመስላችኋል?

**ለ. 'እውነት' ወይም 'ሐሰት' በማለት መልሱ።**

1. ጠጣዋ ነብር ብላ የጮኸችው እውነቷን ነበር።

2. ጠጣዋ ወላጆቿን ሦስት ጊዜ ዋሽታቸዋለች።

3. ጠጣዋ ወጥመዱ ቢይዛትም አልሞተችም ነበር።

4. ጠጣዋ ከጥፋቷ ተምራ ይቅርታ ጠይቃለች።

5. የጠጣዋ ወላጆች መድሀኒት ገዝተው ቀቧት።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ**

## መልመጃ አምስት

**በ 'ሀ' ስር ያሉ ቃላትን በ 'ለ' ስር ካሉት አውዳዊ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተቆራምታ | ሀ. ተከፋ |
| 2. አላቀቁላት | ለ. ቀድሞ እንደምታደርገው |
| 3. ሰርስሮ | ሐ. ልክ ነው አሉ |
| 4. አሸጉላት | መ. ፈርታና አዝና |
| 5. ዞር ብለው | ሠ. አለያዩላት |
| 6. እንደለመደችው | ረ. ተሻላት |

7. አረጋገጡ
8. አዘኑ
9. ተደብቃ
10. ዳነላት

ሰ. በወላጆቿ ሳትታይ
ሽ. ሸፈኑላት
ቀ. ወደ ኋላ አይተው
በ. በደንብ ወደ ውስጥ ገብቶ

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

### ተግባር አራት

**ቀጣዩን ምንባብ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ተራ በተራ አንብቡ።**

#### ጥሩ ስነምግባር ያላቸው ልጆች

ጥሩ ስነምግባር ያላቸው ልጆች ታላላቆቻቸውን ያከብራሉ፣ ታናናሾቻቸውን ይወዳሉ። ባለ ጥሩ ስነምግባር ልጆች አይዋሹም፣ የሌሎች የሆነውን አይፈልጉም፣ ከማንም ጋር አይጣሉም፤ ጓደኞቻቸውንም አይሳደቡም፤ ከሰዎች ጋር ተስማምተው ይኖራሉ፤ ወይም አይጣሉም። ባለ ጥሩ ስነምግባር ልጆች በሌሎች ላይ ክፉ ነገር አይፈፅሙም፤ ሲፈፀምባቸውም ዝም አይሉም። መልካም ስነምግባርን የተላበሱ ልጆች ጊዜያቸውን በአግባቡ ይጠቀማሉ፣ለወላጆቻቸውና መምህራን ይታዘዛሉ፣ ትምህርታቸውንም በትኩረት ይከታተላሉ።

**በምንባቡ ውስጥ የተዘረዘሩትንና የጥሩ ስነምግባር ባለቤት ልጆች መገለጫዎችን ባጭር ባጭሩ ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።**

**ምሳሌ፡** ጥሩ ስነምግባር ያላቸው ልጆች፡-

- ታላላቆቻቸውን ያከብራሉ፤
- ታናናሾቻቸውን ይወዳሉ፤

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ ስድስት

**በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡት ቃላት እና ሀረጋትን ጥሩ ወይም መጥፎ ባህሪ መሆናቸውን በመለየት መድቧቸው። ምሳሌውን እዩ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትሁት | ሰው አክባሪ | ተሳዳቢ | አኩራፊ |
| ተጫዋች | ታዛዥ | ውሸታም | ተወዳጅ |
| አጭበርባሪ | ታማኝ | አታላይ | ትጉህ |
| ጠንካራ | ሰነፍ | ጎበዝ | |

| ጥሩ(ሰናይ) ባህሪያት | መጥፎ(እኩይ) ባህሪያት |
|---|---|
| - ትሁት | - ተሳዳቢ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ሰባት

**ቀጥሎ ለተዘረዘሩ ቃላት ተቃራኒ ፈልጉላቸው::**

ውሸታም ⟶ ሀቀኛ

አታላይ ⟶ ታማኝ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጤናማ | ልጅነት | ያልተማረ | ቁምነገር |
| መጥላት | ጠቃሚ | ቅሬታ | አለመታዘዝ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ስምንት

**ተገቢ የሆኑ ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም የሚከተሉትን አረፍተነገሮች መልሳችሁ ፃፏቸው።**

**ምሳሌ፡-** *ሀ. እኔ ወደ ትምህርት ቤት እየሄድኩ ነው።*

*(አራት ነጥብ)*

*ለ. በእግር፣ በባጃጅ ወይም ታክሲ እንጓዛለን።*
*(ነጠላ ሰረዝ፣ አራት ነጥብ)*

1. ጌጤ ሰው አክባሪ ልጅ ናት
2. ሂርኮ ፀዳለ አሳንቴና ቴዎድሮስ ጓደኞሞች ናቸው
3. ሶፊያ በትምህርቷ አንደኛ ወጣች

4. ወደ ቤተ መፅሐፍ ለምን እንሄድም

5. ወረቀት እርሳስና ማስመሪያ ያስፈልጉኛል

6. መሳደብ የጥሩ ልጅ ባህሪ አይደለም

7. ዛሬ ክፍል ያልመጣው ማነው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

**ተግባር አምስት**

**ዛሬ ትምህርት ቤት ስትመጡ መንገድ ላይ ያያችኋቸውን ነገሮች በተመለከተ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ አረፍተነገሮች ፃፉ።**

**ምሳሌ፡**1. ልጆች ሜዳ ላይ ኳስ ይጫወታሉ።

2. ወደ ሱቅ ተልካ የምትሄድ ልጅ አይቻለሁ።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

## መልመጃ አስር

**ሀ. ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ ተከታዮቹን አረፍተነገሮቹ መልሳችሁ ፃፏቸው።**

**ምሳሌ፡** 1. “እኔ በቦታው አልነበርኩም” አለች።

2. የዛሬው ቀንስ በጣም ደስ ይላል!

3. ወደ ቤት እሄዳለሁ፤ ምሳዬን እበላለሁ።

1. በርትቼ አጠናለሁ አንደኛ እወጣለሁ

2. እንዴት የምታምር አበባ አየሁ መሰለሽ

3. መቼ ትመጣለህ አለችኝ
4. ጤፍ በቆሎ ስንዴ እና ገብስ የእህል ዘር ናቸው
5. ለምን ጠራሽኝ
6. ገበያ እንሄዳለን እህል እንሸምታለን
7. ልዩነታችንን በውይይት መፍታት ይገባናል
8. ተረት እንቆቅልሽና አፈ ታሪክ ስነቃል ናቸው

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ለ. ተከታዮቹን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም ሁለት ሁለት አረፍተነገሮች ፅፋችሁ ክፍል ውስጥ አንብቡ።**

? ። ፤

# ምዕራፍ ሰባት፡ ግብርና

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በትምህርት አንድ ስር በመምህራችሁ የሚነበብላችሁ 'አንበሳና ዝሆን' የተሰኘ የማዳመጥ ምንባብ ቀርቧል። በምንባቡ መሠረትም መልመጃዎችና ተግባሮች ተሰጥተዋል። ትዕዛዛቱን እየተከተላችሁ ስሯቸው።**

**የእነዚህን ቃላት ፍቺ ገምቱ።**

ሀብታም ስጋ በል አሰራር አርዓያነት

## አንበሳና ዝሆን

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ስለ አንበሳና ዝሆን የምታውቁትን ተናገሩ::
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የዱር እንስሳትን ስም ጥቀሱ።

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በተደመጠው ትረካ መሰረት መልሱ።**

1. የአንበሳና ዝሆን ግንኙነት ምን ነበር?
2. አንበሳ አስቀድሞ የተሰማራው በ ____________ ስራ ሲሆን በኋላ ወደ ____________ ተመለሰ።
3. የዝሆን የቀድሞ ስራ ____________ ሲሆን በኋላ ላይ በ____________ስራ ተሰማራ
4. 'ስራና ሰሪ ተገናኙ…' ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. ለልመናና ለብድር የሚመጣ እንስሳ ለምን ጠፋ?
6. ከአዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተማራችሁ?

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### ተግባር አንድ

**ታሪኩን መልሳችሁ በአጭሩ በቃል ተናገሩ። ሌሎቻችሁ ተራችሁ እስኪደርስ በጥሞና አዳምጡ።**

ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር ሁለት

**ቀጣዩን ምልልስ አጥኑና ገበሬና ነጋዴ በመሆን የሚና ጨዋታ ተጫወቱ።**

## ገበሬና ነጋዴ

**ነጋዴ፡** *እንደምን ዋሉ አያ ገበሬ?*

**ገበሬ፡** *እንደምን ዋሉ አያ ነጋዴ?*

**ነጋዴ፡** *ዛሬ የሚሸመት ምን ይዘዋል?*

**ገበሬ፡** *እኛ ጋ ምን ይጠፋል ብለው ነው?! ሁሉ በየአይነቱ አለ። እህል ቢሉ ጥራጥሬ፣ አትክልት ቢሉ ፍራፍሬ!*

**ነጋዴ፡** *አዎና ገበሬ ጋ ድሮስ ምን ጠፍቶ፤ ዶሮ ቢሉ በግ፣ ፍየል ቢሉ በሬ፤ ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ!*

**ገበሬ፡** *ልክ ብለዋል፤ የአገር ዋልታና ማገር ማለት እኛ ነን!*

**ነጋዴ፡** *በትክክል! በሉ አሁን የሚቆጠረውን ቆጥረው፣ የሚመዘነውን መዝነው ይስጡኝ። ከተሜ ሸማቹ እየጠበቀኝ ነው ቶሎ ልሂድ።*

**ገበሬ፡** *ይሁና ይሄው ባይነት ባይነቱ! እኛስ ሰው ሸምቶ ሲበላልን አይደል ደስታችን! አላግባብ ግን ዋጋ አትጨምሩባቸው። ታልሆነ እኛው ደጃቸው ድረስ እናቀርብላቸዋለን።*

**ነጋዴ፡** *አያስቡ ችግር የለም፣ እኛስ ሸማቹ ከሌለ ምን መድረሻ አለን ብለው ነው? ሁሉንም በተመጣጣኝ ዋጋ እናደርሳለን።*

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**መልመጃ ሁለት**

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁባቸው በኋላ በተወካያችሁ አማካኝነት የቃል ዘገባ አቅርቡ።**

1. ገበሬና ነጋዴ መጀመሪያ ሲገናኙ ያደረጉት ምንድን ነው?
2. ‘ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ’ የተባለው ለማን ነው?

3. ነጋዴ ዋጋ የሚያስወድድ ከሆነ ገበሬ ምን እናደርጋለን አለ?
4. ነጋዴውን የሚጠብቀው ማን ነው?
5. ገበሬና ነጋዴ ሸማቹን በተመለከተ የተስማሙት በምን ላይ ነው?
6. የአገር ዋልታና ማገር የተባለው ማነው?

ክፍለጊዜ፡ ስድስት

## ተግባር ሦስት

**በአካባቢያችሁ ምን አይነት የግብርና ስራ እንደሚሰራ ወላጆቻችሁን ወይም የአካባቢያችሁን ሰው ጠይቁ። ያገኛችሁትን መረጃም አደራጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ።**

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ተግባር አራት

**የሚከተለውን መዝሙር ከመምህራችሁ ጋር ተለማመዱና ዘምሩ።**

ግብርናዬ ግብርናዬ

ዋልታዬ ነህ መመኪያዬ

ግብርናዬ ግብርናዬ

የስራ አውራ መቆያዬ።

የዶሮ እርባታ፣ የበግ ጠቦቱ

የሆነልህ ነህ፣ ሁሉ ከቤቱ።

ግብርናዬ ግብርናዬ

ዋልታዬ ነህ መመኪያዬ

እንቁላል ስጋ ቢያሻኝ ልበላ

ካንተ ዘንድ ነው ሁሉ ሚደላ።

ግብርናዬ ግብርናዬ

የስራ አውራ መቆያዬ።

ከብት ማደለብ፣ ወተቱን ማለብ

ሰብሉ ባይነቱ፣ ንቡንም ማነብ

ግብርና ባንተ ቀረልኝ መራብ

ግብርናዬ ግብርናዬ

ዋልታዬ ነህ መመኪያዬ

ግብርናዬ ግብርናዬ

የስራ አውራ መቆያዬ።

ግግግ ግግግ ብብብ ብብብ

ርርር ርርር ናናና ናናና!

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## መልመጃ ሦስት

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በጥንድ ተወያይታችሁ በቃል ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ።**

1. **'የስራ አውራ'** ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?
2. **'ሁሉ ሚደላ'** የሚለውን አገላለፅ የሚተካ ሀረግ ስጡ።
3. በግብርና **'መራብ የሚቀረው'** እንዴት ነው?
4. ግጥሙ ለግብርና ያለው ምልከታ **አወንታዊ** ነው ወይስ **አሉታዊ**? ምክንያት ስጡ።
5. በመዝሙሩ (በግጥሙ) መሰረት ግብርና ምን ምን ስራዎች እንደሚካተቱበት ዘርዝሩ።

ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### ዘመናዊና ባህላዊ ግብርና

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ስለግብርና የምታውቁትን ተናገሩ?

2. በአካባቢያችሁ ምን አይነት የግብርና ስራ ይሰራል?

3. የእነዚህን ቃላት ፍቺ ገምቱ፡፡

ተደራሽ ቴክኖሎጂ ግብዓት አሰራር

የግብርና ስራን ባህላዊና ዘመናዊ ብለን በሁለት ልንከፍለው እንችላለን። ባህላዊ ግብርና ከጥንት ጀምሮ ሲተገበር የነበረ ነው። በባህላዊ ግብርና የእንስሳትና የሰው ጉልበት ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን፣ አድካሚና አነስተኛ ምርት የሚያስገኝ ነው። ባህላዊ ግብርናን በብዛት የሚተገብሩ አገራት ዜጎቻቸውን ለመመገብ እንኳ ይቸገራሉ። ምንም እንኳ ባህላዊ ግብርና ተደራሽነቱ ሰፊ ቢመስልም፣ ብዙ የሰው ሀይል የሚጠይቅና ምርታማነቱም ዝቅተኛ የሆነ ነው። እንዲሁም ብዙ ጊዜ ምርት ያለአግባብ እንዲባክን ያደርጋል። ከዚህም ሌላ ባህላዊ ግብርና በወቅቶች ላይ ጥገኛ የሆነ ነው ማለት ይቻላል። ለምሳሌ ለእህል ምርት የዝናብ ወቅት ይጠበቃል።

*1. የግብርና ስራ በስንት ይከፈላል?*

*2. ቀጣዩ አንቀፅ ስለምን የሚነግረን ይመስላችኋል?*

በአንፃሩ ዘመናዊ እርሻ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የፈጠራ ስራዎችን ጥቅም ላይ የሚያውል በመሆኑ አሰራሩ

የተቀላጠፈ ነው። በዘመናዊ ግብርና ምርት ከፍ ይላል፤ ጊዜም ከብክነት ይድናል። ከዚህም በላይ አላግባብ ይባክን የነበረው የሰው ጉልበት ይቆጠባል። ምርት በሚያስገኙ ግብዓቶች ላይ ሁልጊዜ ማሻሻያዎች ስለሚደረጉ፣ በጥቂት ቦታዎችና በውስን ሀብቶች አመርቂ ውጤት ይመዘገባል። በሌላ በኩል ዘመናዊ ግብርና በወቅቶች ላይ ብቻ ጥገኛ አይሆንም። በራሱ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ የተለያዩ ምርቶች በጊዜ ሳይገደቡ ይመረታሉ።

ክፍለጊዜ፡ አስር

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

**ወደምንባቡ ተመልሳችሁ በማሰስ ባዶ ቦታዎቹን በተገቢ ቃላት ሙሉ።**

1. የግብርና ስራ __________እና__________ተብሎ በሁለት ይከፈላል።
2. ከጥንት ጀምሮ ሲተገበር የነበረው________ነው።
3. ባህላዊ ግብርናን በብዛት የሚተገብሩ አገራት ዜጎቻቸውን__________ይቸገራሉ።

4. ብዙ ጊዜ ምርት ያላግባብ እንዲባክን የሚያደርገው__________ነው።
5. ባህላዊ ግብርና ብዙ የሰው ሀይል__________ ምርታማነቱም __________።
6. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የፈጠራ ስራዎችን የሚጠቀመው __________ነው።
7. በዘመናዊ ግብርና በጥቂት ቦታዎችና በውስን ሀብቶች __________ ውጤት ይመዘገባል።
8. ዘመናዊ ግብርና በራሱ__________ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

### መልመጃ አምስት

**ተከታዮቹን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ።**

1. ከአንቀፅ አንድ ምን ቁም ነገር አገኛችሁ?
2. በአንቀፅ ሁለት ውስጥ የተጠቀሱት ዋና ዋና ነጥቦች ምን ምን ናቸው?
3. ብዙ የሰው ሀይል የሚጠይቀውና ምርታማነቱ ዝቅ ያለው የትኛው የግብርና አይነት ነው?
4. ጊዜ የማይባክንበትና ከፍ ያለ ምርት የሚያስገኘው የትኛው አይነት ግብርና ነው?

5. ግብርና ስራ ላይ የመሳተፍ እድሉ ቢገጥማችሁ የትኛውን አይነት ትመርጣላችሁ? ለምን?

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ ስድስት

**ሀ. ተከታዮቹን ቃላት/ሀረጋት ከተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ። አገባባቸውን ከተግባር አንድ ተመልከቱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መዘረፍ | ሀ. ማስወደድ |
| 2. ተመጣጣኝ | ለ. ውለታ ቢስ |
| 3. ሽማች | ሐ. መቀበል |
| 4. አመድ አፋሽ | መ. ያልተጋነነ |
| 5. ዋጋ መጫን | ሠ. መቀማት |
| 6. መረከብ | ረ. ገዢ |

**ለ. ግብርናዬ የሚለውን መዝሙር መሰረት በማድረግ ተከታዮቹን ቃላት ከፍቺያቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መቆያዬ | ሀ. የሚመች |
| 2. ማደለብ | ለ. መኖሪያዬ |

3. መመኪያዬ ሐ. ብፌልግ
4. ቢያሻኝ መ. ማወፌር
5. የሚደላ ሠ. መተማመኛዬ

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

**ተግባር አምስት**

**ሀ. አስቀድማችሁ ወላጆቻችሁን ወይም ከጎረቤታችሁ ሰው ጠይቃችሁ ቀጣዮቹን ጥያቄዎች መልሱ።**

የላም ልጅ ጥጃ ይባላል።

1. የፈረስ ልጅ __________ተብሎ ይጠራል።
2. የውሻ ልጅ __________ ይባላል።
3. የአህያ ልጅ __________ተብሎ ይጠራል።
4. የአንበሳ ልጅ __________ ይባላል።
5. የድመት ልጅ ________ ተብሎ ይጠራል።
6. የዶሮ ልጅ __________ ይባላል።
7. የበግ ልጅ __________ ተብሎ ይጠራል።

**ለ. በምሳሌው መሰረት ቀሪዎቹን አሟሉ።**

ማርባት መዝራት ማቆር ማረስ መትከል ማልማት

**ምሳሌ፡** ለንብ ማነብ ስንል፣ ለዶሮ ማርባት እንላለን፡፡

1. ለእርሻ _______ ስንል፣ ለውሃ ________ እንላለን::

2. ለእንስሳት______ ስንል፣ ለሰብል ______ እንላለን::

3. ለዛፍ _______ ስንል፣ ለእህል _______ እንላለን::

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

### መልመጃ ሰባት

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላት ትኩረት ሰጥታችሁ አንብቧቸው።**

1. ምርቱ ፈጥኖ ደርሷል።
2. ደራርቱ ምንኛ ታድላለች።
3. ወንድሜ ትናንት መጣ።
4. ተወዳዳሪዋ ክፉኛ ወደቀች።

ከላይ የተሰመረባቸው ቃላት በሙሉ ተውሳከ ግሶች ወይም የግስ ገላጭ ናቸው።

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ፃፉና ተውሳከ ግሶቹን ለይታችሁ አስምሩባቸው።**

1. አባቴ ውጪ ተቀመጠ።
2. እናቴ ቅድም ሄደች።
3. ፈረሰኛው ወዲህ መጣ።

4. ዶክተሯ ክፉኛ አዘነች።
5. አምቡላንሱ በፍጥነት ደረሰ።
6. ፍራፍሬው በደንብ በሰ৷ል።

**ተውሳከ ግሶች፡ ግስ ላይ የሚጨመሩ ቃላት ናቸው። በአረፍተ ነገር ውስጥ ከግስ ጋር እየገቡ ግሱ የሚገልፀው ድርጊት እንዴት፣ መቼ፣ ለምን፣ በምን ሁኔታ እንደተፈፀመ ይነግሩናል።**

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

### መልመጃ ስምንት

**በተከታዮቹ አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ተውሳከ ግሶች ምንን እንደሚገልጹ አስረዱ።**

**ምሳሌ፡- አገራችን ጥንታዊት ናት። (ጊዜን)**

**ቶሎ ቶሎ ተራመድኩኝ። (ሁኔታን/ፍጥነትን)**

1. ጠጣዋ ዛፍ ላይ ወጣች።
2. ባቡሩ በቀስታ ሄደ።
3. ዝናቡ ክፉኛ ዘነበ።

4. እህቴ ቅድም መጣች።
5. መፅሐፍሽ እዚያ አለ።
6. አውቶቢሱ ገና አልተነሳም።
7. ሆዱን በጣም አመመው።
8. ኳሷን ጅልኛ ጠለዘኳት።
9. ልብሳችን ሳጥኑ ውስጥ ተቀምጧል።
10. ማጥናት ዛሬ ነው።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት**

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ዘጠኝ

**ተከታዮቹን ተውሳከ ግሶች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ትናንት | ክፉኛ | አሁን | ቤት ውስጥ | እዚህ |
| ምንኛ | በጣም | የዛሬ ሳምንት | በዝግታ | |

**ምሳሌ፡** ወንድሜ የዛሬ ሳምንት ይመጣል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስር

**የሚከተለውን አንቀፅ አንብቡና ዋናውን ሀሳብ ፅፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አጋሩ።**

ለትራፊክ አደጋ መከሰት ዋነኛ ምክንያቶች ራሳቸው አሽከርካሪዎች ናቸው። አሽከርካሪዎች የመንገድ ምልክቶችን እያዩ፣ በተፈቀደ ፍጥነት ማሽከርከር ሲገባቸው፣ ከልክ በላይ በመፍጠን ለጉዳት ይዳረጋሉ። በከፍተኛ ፍጥነት የሚያሽከረክሩ ሹፌሮች በድንገት ከፊት ለፊታቸው እንስሳ ወይም ሰው ቢገባባቸው መኪናውን መቆጣጠር አይችሉም። በዚህም ምክንያት ራሳቸውንና ሌሎችን ለጉዳት ይዳርጋሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### መልመጃ አስራ አንድ

**ሳጥኑ ውስጥ የተሰጧችሁን ቃላት በማሰካካት አረፍተ ነገር መስርቱ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| የአካባቢ | የዱር | መጠበቅ | ገነባው |
| አናጢው | ተማሪ | ሁልጊዜ | ይገባል |
| ሰረገላ | ዘመናዊ | አስውቦ | ያጠናል |
| ቀጭኔ | ቤቱን | እንስሳ | ነው |
| ጎበዝ | ባህላዊ | መጓጓዣ | |
| አውሮፕላን | ንፅህናን | | |

# ምዕራፍ ስምንት፡ ስራ

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ክፍል መምህራችሁ “ሰነፉ ፌንጣና ጉንዳን” በሚል ርዕስ ምንባብ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡ። ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግም መልመጃዎችና ተግባራቱን ስሩ።




### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ጉንዳንን በምን ታውቋታላችሁ?
2. ፌንጣ ባከባቢያችሁ ሌላ መጠሪያ አለው?
3. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ገምቱ።

| አብዝቶ | ማሰስ | ደን | ስንቅ |
|---|---|---|---|

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት 'እውነት' ወይም 'ሐሰት' በሉ።**

1. ፌንጣ ስራ መስራት የሚወድና ጎበዝ ነበር።
2. ጉንዳን ለፌንጣው ለክረምቱ ተዘጋጅ ብላዋለች።
3. ፌንጣ የሚኖረው በተራራማ ዋሻ ውስጥ ነው።
4. ጉንዳን የብርቱ ፌንጣ የደካማ ምሳሌ ናቸው።
5. ጉንዳን ለፌንጣ ወዲያው ምግብ አቅርባለታለች።

**ለ. የተጓደሉትን ቃላትና ሀረጋት አሟሉ።**

1. ፌንጣና ጉንዳኔ ___________ ነበሩ።
2. ጉንዳኔ ቀኑን ሙሉ ___________ ትውላለች።
3. ፌንጣ በጣም ___________ ይወዳል።
4. ክረምቱ ሲመጣ ጉንዳኔ ብዙ ________ ነበራት።
5. ክረምቱ ሲመጣ ፌንጣ ________ አልነበረውም።

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### መልመጃ ሁለት

**በተደመጠው ምንባብ መሰረት ተከታዮቹን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የጉንዳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ልክ ነው ትላላችሁ?
2. መሰሎቿ የተባሉት እነማን ናቸው?
3. 'በጋ በጋ ሆኖ የማይቀረው' ለምንድን ነው?
4. ጉንዳን 'ያኔኮ ነግሬህ ነበረ' ያለችው ምኑን ነው?

### መልመጃ ሦስት

**ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ፈልጉ። ምላሻችሁንም ከጓደኞቻችሁ ጋር አነፃፅሩ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| መሞርመር | መድረሻ | መጎሳቆል | ስንቅ |
| ማንጓጠጥ | ማሰስ | ማጓጓዝ | ሰነፍ |

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች ያሉትን ስዕሎች አጥኑና በምስሉ ላይ የሚታዩት ሰዎች በምን በምን ሙያ እንደተሰማሩ ተናገሩ። አንደኛው ሙያ ከሌላኛው ጋር ያለውን ግንኙነትም አሳዩ።**



## ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር ሁለት

በትርፍ ጊዜያችሁ ምን ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ? የምታከናውኗቸውን ተግባራት ፃፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘገባ አቅርቡ።

| የተማሪዎች ትርፍ ጊዜ አጠቃቀም መርሃግብር ናሙና | | |
|---|---|---|
| ከ11፡00 - 12፡30 | ከ12፡30-2፡30 | ከ2፡30- 3፡00 |
| ቤተሰብ ማገዝ | ራት መብላት | ማጥናት |
| ጨዋታ | ዕቃ ማጠብ | |
| የቤት ሥራ መስራት | ዜና ማዳመጥ | |

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ተግባር ሦስት

ከታች በተሰጣችሁ ምሳሌ መሠረት ወደፊት መሆን የምትፈልጉትን ተናገሩ።

| መሆን የምፈልገው (ዕቅድ ሀ) | ለምን? | እንዴት አሳካዋለሁ? | ባይሳካስ? (እቅድ ለ) |
|---|---|---|---|
| | | | |

**ምሳሌ፡**

**መሆን የምፈልገው፡** *እኔ ወደፊት መሆን የምፈልገው የእንስሳት ሀኪም ነው።*

**ምክንያት፡** *ምክንያቱም በአካባቢያችን በርካታ የቤት እንስሳት አሉ።*

**እንዴት?** *ምርምር በማድረግ የተሻለ ምርት እንዲሰጡ አደርጋለሁ። ይህንንም ትምህርቴን ባግባቡ በመከታተል አሳካለሁ።*

**አማራጭ ዕቅድ (ዕቅድ ለ)፡** *ይህ ባይሳካልኝ ደግሞ ሌላኛው ምርጫዬ የመስኖ ባለሙያ መሆን ነው።*

ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ተግባር አራት

በሁለት ቡድን ተቧደኑና አንዱ ቡድን ከዚህ በታች ካሉት ቃላት አንዱን ሲጠራ ሌላኛው ቡድን በቃሉ አጭር ዐረፍተነገር ይመሠርታል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጊዜ | መጫወት | አነባለሁ | እረዳለሁ | ስራ |
| ሮጠች | አስተማሪ | ሀኪም | መጡ | ገዛ |

ክፍለጊዜ፡ ስምንት

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

## ትጉኋ መምህርት



### የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ሰዎች ምን ምን ስራ ይሰራሉ?
2. የተከታዮቹን ቃላት ፍቺ ገምቱ።

**ሙያ ባግባቡ ትጉህ መገሰፅ**

መምህርት ቦንቱ በአስተማሪነት ተቀጥራ ትሰራለች። ለስራ ከቤቷ የምትነሳው አንድ ሰዓት ላይ ሲሆን፣ ለመጓጓዣነት ታካሲ ትጠቀማለች። መምህርት ቦንቱ ትምህርት ቤት ከደረሰች በኋላ የሰንደቃላማ ማክበር ስነስርዓትን ታስተባብራለች። ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆንም ለማስተማር ክፍል ውስጥ ትገኛለች። ክፍለጊዜዎቿንም ባግባቡ ተጠቅማ የእለት ስራዋን ታከናውናለች።

*1. መምህርት ቦንቱ የተቀጠረችው በምን ሙያ ነው?*

መምህርት ቦንቱ በተማሪዎቿ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ትጉህ ሰራኛ ናት። ጊዜዋን ሁሉ ተማሪዎቿን ለመርዳት ታውላለች። የተለያዩ ተግባራትን ትሰጣቸዋለች፤ እንዴት መስራትና ማጥናትም እንዳለባቸው ትነግራቸዋለች። የቤት ስራ የማይሰሩና የሚያረፍዱ ተማሪዎችን ትገስፃቸዋለች። በዚህም ጥቂት የማይባሉ ተማሪዎች ከመጥፎ ልማዳቸው እንዲታረሙ አድርጋለች።

*2 መምህር ቦንቱ ለተማሪዎቿ ምን ትነግራቸዋለች?*

መምህርት ቦንቱ ከስራ ባልደረቦቿ ጋር ተስማምታ መስራትን የተካነች ናት። አዳዲስ መምህራንና ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቱ ሲመጡም በአክብሮት ትቀበላቸዋለች። እነዚህ ተግባሮቿም በትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅ አድርገዋታል።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

**ምንባቡን ደግማችሁ አንብቡትና የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ::**

1. ‘መጥፎ ልማድ’ የተባለው ምንድን ነው?
2. መምህርት ቦንቱ ተማሪዎቿን ከመጥፎ ልማዳቸው ያላቀቀቻቸው እንዴት ነው?
3. መምህርት ቦንቱ አዳዲስ መምህራንና ተማሪዎች ሲመጡ እንዴት ትቀበላቸዋለች?
4. “መምህርት ቦንቱ በተማሪዎቿ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ትጉህ ሰራኛ ናት::” ለምን ተባለች?

ክፍለጊዜ፡ አስር

## መልመጃ አምስት

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስጧቸው።

ምሳሌ፡- ትገስፃቸዋለች = ጥፋቱ እንዳይደገም ትመክራቸዋለች

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትገስፃቸዋለች | መጓጓዣ | ባግባቡ | የተካነ |
| ባልደረቦቿ | የሚያረፍዱ | ትጉህ | ታከናውናለች |

ለ. ከላይ ፍቺ በሰጣችኋቸው ቃላት አረፍተነገር መስርቱ።

ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### ተግባር አምስት

የተከታዮቹን ቃላት ፍቺ ለማወቅ ሰዎች ጠይቁ ወይም መዝገበ ቃላት ተመልከቱ። ያገኛችሁትን ምላሽ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| መተግበር | ዕቅድ | አፈፃፀም | መስተጓጎል |
| አመርቂ | ስኬት | ትርፋማ | ተግዳሮት |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

### መልመጃ ሰባት

**ሀ. ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

1. አረፍ እያልንም ስለትምህርት ቤት ውሏችን እናወራለን።
2. ከዚያም ቤት ያፈራውን እቀማምሳለሁ::
3. የትምህርት መሳሪያዎቼን አሰናዳለሁ።
4. ተሰነባብቼ ጣፋጭ ህልሜን እያየሁ ለሽ እላለሁ!
5. ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር ለመጫወት እሄዳለሁ።

**ለ. ከላይ አውዳዊ ፍቺ የሰጣችኋቸውን ቃላት በመጠቀም የየራሳችሁን አረፍተ ነገሮች መስርቱ።**

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት

### መልመጃ ስምንት

**ሀ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉ ቅጥያዎችን ለይታችሁ አመልክቱ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስለሰው | አክባሪነት | አልጠግም | አልዋሽም |
| ሞኝነት | ለመሄድ | ስለቀረ | ለመስራት |

**ምሳሌ፡-** ልጅነት = ልጅ - ነት

አልበላም = አል- - ም

ለመብላት= ለ- መብላት

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

**ለ. በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ከሚገኙ ቃላት ቅጥያ ያላቸውን ለይታችሁ አመልክቱ።**

1. ለፈተና እየተዘጋጀሁ ነው፡፡
2. ከገበያ ስትመጣ እመንገድ ላይ አስቆመቻት፡፡
3. የትራፊክ አደጋ ባለመጠንቀቅ ይከሰታል፡፡
4. አቶ ሁሴን ክፉ አልተናገሩም፡፡
5. ሰውነታችንን ሁልጊዜ መታጠብ አለብን፡፡
6. ኳስ መጫወት አካላዊ ጥንካሬ ይሰጣል፡፡

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

**ሐ. በምሳሌው መሰረት ቅጥያዎችን በመጨመር ቃላት መስርቱ። ቃላቱን በራሳችሁ ምረጡ፡፡**

የ- እኔ = የእኔ    ለ- መሄድ = ለመሄድ

የ- ስራ = የስራ    ስለ- ስራ = ስለስራ

አል- መጣ -ም = አልመጣም

ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### አያያዥ ቃላት

**መልመጃ ዘጠኝ**

**ተገቢውን አያያዥ በመምረጥ አረፍተ ነገሮቹን አሟሉ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እንጂ | ወይም | ሆኖም | እና | ይሁን እንጂ |

**ምሳሌ፡**

*እርሳሴን ጥዬዋለሁ ________ ለጓደኞቼ አውሻቸዋለሁ።*

*እርሳሴን ጥዬዋለሁ ወይም ለጓደኞቼ አውሻቸዋለሁ።*

1. ከሁለት አንዳችን አንቀርም፤ እኔ ________ እህቴ እንመጣለን።
2. ወደ ትምህርት ቤት ስሄድ ደብተሬን ________ መፅሐፍቶቼን እይዛለሁ።
3. በደንብ አጥንቶ ነበር ________ ፈተናውን አላለፈም።
4. በደንብ ተዘጋጅታ ነበር ________ እቅዷን ተግባራዊ አላደረገችም።
5. ሊዘገይ ይችል ይሆናል ________ አይቀርም።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስር

**በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ያሉ ሀሳቦችን በማያያዝ ወደ አንድ አረፍተ ነገር መልሷቸው።**

**ምሳሌ፡***ስራ አይሰራም። ገንዘብ ማግኘት ይፈልጋል።*

*ስራ አይሰራም ነገር ግን ገንዘብ ማግኘት ይፈልጋል።*

1. ሰብለ ወደ ሀገሯ ለመመለስ ወስናለች። ሰብለ ጓዟን አሰናድታለች።
2. ታሲሳ ወደ ኢሉባቦር ይሄዳል። ታሲሳ ወደ ቦረና ይሄዳል።
3. ኬሪያ ሽቀጣሽቀጥ ትሸጣለች። መገርቱ ሽቀጣሽቀጥ ትሸጣለች።
4. ብሩህ ቀን ደስ ይለኛል። ፀሐያማ ቀን ደስ ይለኛል።
5. እናቴ ናፍቃኛለች። ስልክ እደውልላታለሁ።
6. ዛፍ መትከል አለብን። በአየር ሙቀት መጨመር የተነሳ እንጠፋለን።
7. ጠንክሮ መስራት ያስከብራል። ሌብነት ያሳፍራል።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት

### መልመጃ አስራ አንድ

**አያያዦችን በመጠቀም የየራሳችሁን አረፍተነገሮች መስርቱ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ግን | ስለሆነም | ሆኖም | ነገር ግን |
| እና | ወይም | ስለዚህ | በዚህ የተነሳ |

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ባህል



## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ይህ ትምህርት ማዳመጥን ለማስተማር የተዘጋጀ ነው። ለዚህም ምንባብ፣ የተለያዩ ተግባራትና መልመጃዎች ቀርበዋል። ትዕዛዛቱን በመከተል ተግብሯቸው።

### እንቆቅልሽ

#### ተግባር አንድ

መምህራችሁ ስለእንቆቅልሽ የሚሰጡትን ገለፃ አዳምጡ። ገለፃውን ካዳመጣችሁ በኋላም እንቆቅልሽ በመጠየቅና በመመለስ ተሳተፉ።

**ምሳሌ፡-**

ታሪኳ፡ እንቆቅልሽ

ሲፈን፡ ምናውቅልሽ

ታሪኳ፡ ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ


ሲፈን፡ የቤት አጥር

ታሪኳ፡ አላወቅሽውም፤ እንደገና ሞክሪ።

ሲፈን፡ እሺ....እ... አይን!

ታሪኳ፡ ጎበዝ መልሰሻል።

ሲፈን፡ አሁን ተራው የኔ ነው ልጠይቅሽ...






## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

## ንቂው ልጅ

**መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ አዳምጡና ጥያቄዎች መልሱ።**

### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከላይ ያሉትን ስዕሎች አጥኗቸው።
2. የምንባቡ ታሪክ ስለምን ይመስላችኋል?
3. የቀጣዮቹን ቃላት ፍቺ ገምቱ።

   (*ኩንታል* *አሸለበ* *መቀጣት* *የተጋጠ)*

## ክፍለጊዜ፡ ሦስት

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ::**

1. ዛፍ ስር ቁጭ ብሎ ያሸለበው ማን ነው?
2. በእርግጥ ልጁ አህያውን አይቶታል?
3. ሰውዬው በጣም ደስ ያለው ለምንድን ነው?

4. ልጁ አህያው ማንከሱን፣ አይኑ አለማየቱንና ስንዴ እንደተጫነ እንዴት አወቀ?
5. የንግስቲቱ ፍርድ ልክ ነው ትላላችሁ? እናንተ ብትሆኑ ልጁ ላይ ምን ትፈርዱበት ነበር?
6. ጥያቄዎችን ለመመለስ ማሰብና መመራመር ያለውን ጠቀሜታ ተናገሩ።

**ክፍለጊዜ፡ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

**ተግባር ሁለት**

**በአካባቢያችሁ የሚሰጡ ባህላዊ ህክምናዎችን በተመለከተ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ አሰባስቡና ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ**

**ክፍለጊዜ፡ አምስት**

**ተግባር ሦስት**

**በአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ዘንድ ስለሚታወቅ ባህላዊ ተግባር ወላጆቻችሁን ወይም የአካባቢ ሰዎችን ጠይቁና መረጃ አሰባስቡ። ያሰባሰባችሁትን መረጃ አደራጁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።**

**መረጃችሁ ከሚከተሉት ጉዳዮች በአንዱ ላይ ይሁን፡-**

- ስለገዳ ስርዓት
- ስለምግብ አዘገጃጀት
- ስለጉዲፈቻ
- ስለጥሎሽ (የጋብቻ ጥያቄ)
- ስለባህላዊ አልባሳት (የወንድ ወይም የሴት)
- ስለክብረ በዓላት ወዘተ

**ክፍለጊዜ፡ ስድስት**

### ተግባር አራት

**ጠያቂና መላሽ በመሆን ስለሚከተሉት ቃላት (ባህሪ፣ መልክ፣ ቅርፅ፣ ጥቅም) በመግለፅ የእንቆቅልሽ መጠየቅ አካሄድን ተከትላችሁ ተጠያየቁ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አሳ | ገንፎ | አልጋ | ሙዝ | መኪና |
| ጀበና | ብስክሌት | ሲኒ | መፅሐፍ | ዛፍ |

**ምሳሌ፡ ጠያቂ፡** *እንቆቅልህ*

**መላሽ፡** *ምን አውቅልህ*

**ጠያቂ፡** *ሲበስል ተልጦ የሚበላ፣ መልኩ ቢጫ፣ ውስጡ ቅቤ የሚመስል...*

**መላሽ፡** *ሙዝ*

**ጠያቂ፡** *በትክክል ተመልሷል።*

**ክፍለጊዜ፡ ሰባት**

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### ተግባር አምስት

**ተከታዩን ምንባብ ተራ በተራ ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ እያነበባችሁ ተለማመዱ።**

## ባህል

ባህል የአንድ ማህበረሰብ ማንነትና ህልውና መገለጫ ነው። ምክንያቱም ሰዎች ተለይተው የሚታወቁት በረዥም የጊዜ ሂደት በገነቡት ባህላዊ እሴቶቻቸው ነው። ባህል አኗኗርን፣ አስተሳሰብን፣ አሰራርን፣ አለባበስን፣ አዘፋፈንን፣ አመጋገብን፣ ኪነጥበብንና የማህበረሰቡን ስነፅሑፋዊ ስራዎች ሁሉ ያካትታል።

በአንደኛው ማህበረሰብ ተቀባይነት ያለው ባህል ነክ ጉዳይ በሌላው ዘንድ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል። ይህ ማለት ግን የአንደኛው የተሳሳተ የሌላኛው ደግሞ ያልተሳሳተ ነው ማለት አይደለም። ሁሉም ባህል በየራሱ ልክ ነው።

ስለሆነም ሰዎች የየራሳቸውን ብርቅዬ ባህል አክብረው፣ ጠብቀውና ተንከባክበው ለትውልድ ትውልድ ማሸጋገር ይገባቸዋል።

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

**ተከታዩን ምንባብ በየግላችሁ አንብባችሁ ቀጥለው የመጡትን ጥያቄዎች መልሱ።**

## ቹቹና ጓደኛዋ

ቹቹ ቀና ልጅ ናት። የታመሙትን ትጠይቃለች፤ የተቸገሩትን ትረዳለች። አንድ ቀን ቹቹና ጓደኛዋ ሲጓዙ መንገድ ላይ የወደቀ ቦርሳ አገኙ። ጓደኛዋ አንስታ "ታድለን! በቃ እንክፈተውና የያዘውን ነገር **እንካፈል**" አለች። ቹቹ ግን "**ፈፅሞ** አይሆንም፤ ይህማ **ስርቆት** ነው። ለባለቤቱ መመለስ አለብን።" አለች።

*1. እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?*

ጓደኛዋ ግን "ወድቆ የተገኘ ነገር ይመለሳል እንዴ?" በማለት ልታሳምናት ሞከረች። ቹቹ ግን "ቦርሳው የጠፋበት ሰው በውስጡ ብዙ የሚያስፈልገው ነገር ይኖረዋል። በዚያ ላይ የሰውን ዕቃ ያለ ባለቤቱ ፈቃድ ለራስ ማድረግ በባህላችን **ፀያፍ** ነው" አለቻት።

2. *በባህላችን ፀያፍ ነው የተባለው ምንድን ነው?*

የሆኑ ሴትዮ ከሩቅ "እባካችሁ እዚህ አካባቢ ቦርሳ ያገኛችሁ?" እያሉ መጡ። ሴትዮዋ "የሰው ገንዘብ **አደራ** ተሰጥቶኝ እኮ ነው፤ አሁን **ምን አባቴ ይውጠኛል?**" ይላሉ። ቹቹም "እማማ ወደዚህ ኑ እኛ ወድቆ አግኝተነዋል!" አለች። ሴትዮዋም ሁለቱንም እቅፍ አድርገው ሳሟቸው። **"እናንተን ባይጥልልኝ** ኖሮ የሰው ገንዘብ ከየት አባቴ አምጥቼ እከፍል ነበር?" አሉ በሀዘኔታ። "እደጉ፣ ያሰባችሁት ይሳካ፤ ክፉ አይንካችሁ፤ የራሳችሁን እንጂ የሰው የማትፈልጉ ሁኑ፣" ብለው መረቋቸው። እነቹቹም አሜን አሉ።

**ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ**

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ተከታዮቹን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ መልሱ።**

1. ቹቹ በባህላችን ፀያፍ ነው ያለችው ምኑን ነው?
2. ቦርሷውን የጣሉት ግለሰብ "ምን አባቴ ይውጠኛል?" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?

3. "እናንተን ባይጥልልኝ ኖሮ..." ያሉት ምን ለማለት ነው?
4. ከምንባቡ ታሪክ ምን ተማራችሁ?
5. ሴትዮዋ ምን ብለው መረቋቸው?
6. ሰው ሲመርቀን ምን እንላለን?

## ክፍለጊዜ፡ አስር

**ለ. ታሪኩን በቅደም ተከተል ባጭር ባጭሩ አስቀምጡ**

**ምሳሌ፡-**

- ቹቹና ጓደኛዋ መንገድ ላይ ሄዱ፤
- የወደቀ ቦርሳ አገኙ፤

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

# ትምህርት አራት፡ ቃላት

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. ምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍቺ በሰረት በማድረግ ቃላቱን ከተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ስርቆት | ሀ. አስነዋሪ |
| 2. ይሳካ | ለ. ባይልክልኝ |
| 3. እንካፈል | ሐ. ሌብነት |
| 4. ፀያፍ | መ. እንጋራ |
| 5. ባይጥልልኝ | ሠ. የማይነካ/የሚጠበቅ |
| 6. አደራ | ረ. ይሁን |

ለ. ከዚህ በላይ ካሉት ቃላት አምስቱን መርጣችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡- የሰው አደራ መጠበቅ ይገባል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት**

**መልመጃ አራት**

**እነዚህ አረፍተነገሮች ምን የጎደላቸው ይመስላችኋል?**

1. እርሳሴን ወንበር አገኘሁት።
2. እናቴ ቤት መፅሐፍ እያነበበች ነው።

**ከስር ያሉትን አንብቧቸው። የትኞቹ ቃላት ተጨመሩባቸው?**

1. እርሳሴን ወንበር ስር አገኘሁት።
2. እናቴ ቤት ውስጥ መፅሐፍ እያነበበች ነው።

**መስተዋድድ**

እንደ፣ ወደ፣ ላይ፣ ውስጥ፣ ታች፣ ስር… የመሳሰሉት ቃላት መስተዋድዶች ናቸው። መስተዋድዶች ቃልን ከቃል ያዋድዳሉ ወይም ያዛምዳሉ።

**እነዚህን ሀረጋት አንብቧቸው**

| | | |
|---|---|---|
| ጣሪያው ላይ | ወደ ቤት | በመኪና |
| ክፍሉ ውስጥ | ቢሮ አጠገብ | ከሰፈር |
| እንደእኛ (እንደኛ) | ወንበር ስር | ከወንዙ በታች |

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሦስት**

## መልመጃ አምስት

**በሳጥኑ ውስጥ ካሉት መስተዋድዳዊ ቃላት እየመረጣችሁ ባዶ ቦታውን አሟሉ።**

**እንደ ውስጥ ላይ ታች ስር ውጭ**

1. ቢሮሌና ወንድሟ __________ ገበያ ሄዱ።
2. መርከብ ባህር __________ ይጓዛል።
3. እንቅልፉ ስለመጣ አልጋ _________ ወጥቶ ተኛ።
4. ሱቁ __________ ባህላዊ ለወብሶች ይታያሉ።
5. መጫወቻዬን ከቤት _________ ወድቆ አገኘሁት።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት

## ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ስድስት

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ደብተራችሁ ላይ ፃፉና ባህልን ይመለከታሉ የምትሏቸውን ቃላት ወይም ሀረጋት አስምሩባቸው።**

**ምሳሌ፡**

*ለበአሉ <u>አንሶላ</u> ተዘጋጀልን።*

*<u>የቡና ቀላ</u> ስነስርዓት ተካሄደ።*

1. በብዙ አካባቢዎች በስራ ላይ ዘፈን አለ።
2. ልጃገረዷቱ ፀጉሯን ሹሩባ ተሰርታለች።
3. ጨሌና የሀበሻ ቀሚስ ተገዛልኝ።
4. ሲቄ ሀደ ሲቄ የሚይዙት ቀጭን ዘንግ ነው።
5. እኛ በገዳ ስርዓት እንተዳደራለን።
6. ቁርሳቸውን ገንፎ ወይም ቅንጬ ይበላሉ።

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

### መልመጃ ሰባት

**ተከታዮቹን መስተዋድዶች በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።**

| ወደ | ላይ | ታች | ውስጥ | ስር | እንደ |
|---|---|---|---|---|---|

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስምንት

**የሚከተሉት አረፍተነገሮች የጨጨብሳ ባህላዊ ምግብ አሰራርን የተመለከቱ አረፍተነገሮች ናቸው። ቅደም ተከተላቸው ስለተዛባ አስተካክላችሁ ፃፏቸው።**

ሀ. የተጋገረው በደንብ እስኪበስል ይጠበቃል፤ ሲበስል ይቆራረሳል።

ለ. በተጣደ ድስት ውስጥ ቅቤ፣ በርበሬና ጨው ይጨመራል።

ሐ. ዱቄቱ ከሌሎች ግብዓቶች ጋር ተለውሶ በሸክላ ወይም በብረት ምጣድ ላይ ይጋገራል።

መ. አስፈላጊ ቁሳቁሶች ይዘጋጃሉ።

ሠ. ከዚያም የተቆራረሰው ቂጣ በድስቱ ውስጥ ይገባና እንዲዋሃድ ይታሻል።

ቀ. በመጨረሻም ጨጨብሳ በጥሩ መዓዛ ታውዶ በትኩሱ ይቀርባል።

በ. የጤፍ፣ የስንዴ ወይም የሌላ እህል ዱቄት ይቀርባል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት**

## መልመጃ ዘጠኝ

**ተከታዮቹን ቃላት ወይም ሀረጋት በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ባህላዊ ምግብ | ማረሻ | ጌጥ | ተረት ተረት |
| መከባበር | እንቆቅልሽ | ጋቢ | ቀሚስ |
| ነጠላ | ሽመና | ጠላ | ሹሩባ |

**ምሳሌ፡**

1. እኛ ልጆች እንቆቅልሽ እንጠያየቃለን።
2. ሁሉም ሰው መከባበር አለበት።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

## ተግባር ስድስት

**አንድ በአካባቢያችሁ የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ ምረጡና አዘገጃጀቱን በቅደም ተከተል አጫጭር አረፍተነገሮችን በመጠቀም ፅፋችሁ አቅርቡ።**

**ፍንጭ፡** መጀመሪያ... ከዚያም... ቀጥሎም... እንዲሁም... በመጨረሻም...

# ምዕራፍ አስር፡ ገበያ

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

**በዚህ ትምህርት ክፍል ለማዳመጥ ክሂል ማጎልበቻ የተዘጋጁ መልመጃዎችና ተግባራት ተዘጋጅተዋል። የተሰጡ ትእዛዛትን እየተከተላችሁ ሁሉንም ስሯቸው።**



### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ገበያ ምን ቀን ነው የሚውለው?
2. በገበያው ሰዎች ምን ምን ይገበያያሉ?
3. የተከታዮቹን ቃላት ፍቺ ገምቱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ገበያ | ግብይት | ቴክኖሎጂ | ድረገፅ |

## ክፍለጊዜ፡ ሁለት

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

ሀ. ተከታዮቹን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ንባብ መሰረት እየመረጣችሁ መልሱ።

1. ሰዎች የተለያዩ ነገሮችን ለመግዛትና ለመሸጥ የሚገናኙበት ስፍራ __________ ይባላል።

ሀ. ሆቴል ለ. ስታዲዬም ሐ. ገበያ መ. መናኸሪያ

2. በሀገራችን በብዙ ቦታዎች ግብይት የሚካሄደው፡

ሀ. ትልቅ ዛፍ ስር ለ. ሰፊ ሜዳ ላይ

ሐ. ሱፐር ማርኬቶች ውስጥ መ. ‘ሀ’ እና ‘ለ’

3. የመገበያየትን ታሪካዊ እድገት አስመልክቶ ትክክለኛው ቅደም ተከተል የቱ ነው?

ሀ. ዛፍ ስር፣ መጠለያዎች፣ ሱፐር ማርኬት፣ ድረገፅ

ለ. መጠለያዎች፣ ዛፍ ስር፣ ድረገፅ፣ ሱፐር ማርኬት

ሐ. ድረገፅ፣ ዛፍ ስር፣ መጠለያዎች፣ ሱፐር ማርኬት

መ. ዛፍ ስር፣ ሱፐር ማርኬት፣ መጠለያዎች፣ ድረገፅ

## ለ. በ‘ሀ’ ስር ያሉትን በ‘ለ’ ስር ካሉት ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ወርቅ፣ አሞሌ ጨው | ሀ. ዘመናዊ የፈጠራ ስራዎች |
| 2. ሱፐር ማርኬት፤ድረገፅ | ለ. ባህላዊ መገበያያ ስፍራዎች |
| 3. ዛፍ ስር፤ ሰፊ ሜዳ | ሐ. ዘመናዊ መገበያያ ነገር |
| 4 ገንዘብ ወይም ብር | መ. ዘመናዊ መገበያያ ስፍራዎች |
| 5 መተግበሪያዎች | ሠ. ጥንታዊ መገበያያ ነገሮች |

**ክፍለጊዜ፡ ሦስት**

### መልመጃ ሁለት

**ባዳመጣችሁት ንባብ መሰረት ተከታዮቹን ቃላት ከፍቺያቸው ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መጠለያ | ሀ. መግዛትና መሸጥ |
| 2. ቴክኖሎጂ | ለ. የመገበያያ ስፍራ |
| 3. መገበያየት | ሐ. ውጤቶች |
| 4. ገበያ | መ. አዳዲስ የፈጠራ ስራ |
| 5. ምርቶች | ሠ. ጊዜያዊ መቆያ |

## ክፍለጊዜ፡ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

**ተከታዩን ስዕል ተመልከቱና ምንምን ተግባራት እየተከናወኑ እንዳሉ ለጓደኞቻችሁ አስረዱ።**



## ክፍለጊዜ፡ አምስት

### ተግባር ሁለት

**ይህንን ምልልስ አጥንታችሁ ገዢ እና ሻጭ በመሆን ጭውውቱን ክፍል ውስጥ አቅርቡት።**

**ገዢ፡** *ይሄ ስንት ነው?*

**ሻጭ፡** *አንድ መቶ አስር ብር።*

**ገዢ፡** *የመጨረሻ ዋጋውስ? የምትሸጥበትን ንገረኝ።*

**ሻጭ፡** *በቃ አንድ መቶ አምስት ብር ክፈዪ።*

**ገዢ፡** *መቶ ብር አያዋጣህም? ስለወደድኩት ነው።*

**ሻጭ፡** *ይሄኮ አንደኛው ነው። አምስቷን ጨምረሽ ውሰጂ።*

**ገዢ፡** *ይበቃሃል መቶ ብር፤ ደንበኛ አይደለንም እንዴ?*

**ሻጭ፡** *ይሁን እሺ አምጪ። ስለገዛሽኝ አመሰግናለሁ።*

**ገዢ፡** *እኔም አመሰግናለሁ። መልካም ቀን።*

**ሻጭ፡** *ላንቺም መልካም ቀን።*

## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ተግባር ሦስት


አስቀድማችሁ ዝግጅት አድርጉና ሁለት ሁለት እየሆናችሁ (አንዳችሁ ገዢ ሌላኛችሁ ሻጭ በመሆን) የሚና ጨዋታ ተጫወቱ።

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

### መንገደኞቹና ዛፉ

ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ምንባብ አንብቡና ቀጥለው የተሰጡትን ጥያቄዎች መልሱ።



አንድ ቀን ሁለት መንገደኞች ገበያ ለመሄድ በበረሃ ሲጓዙ የፀሐዩ ሐሩር ስለከበዳቸው አንድ ያረጀና የተወለጋገደ ዛፍ ስር በጅርባቸው ጋደም አሉ። ትንሽ ቆይቶም አንደኛው መንገደኛ የዛፉን ቅርንጫፎች እያመለከተ ለጓደኛው፣ “አየኸው ይህን የማይረባ ዛፍ፤ ምንም የሚበላ ፍሬ የለውም፤ ግንዱን እንኳ ብንቆርጠው ምንም ጥቅም የሚሰጠን አይደለም።” በማለት ተናገረ።

ንግግራቸውን በጥሞና ያዳመጠው ዛፍም “ውለታ ቢስ ባትሆኑ ጥሩ ነው፤ በዚህች ወሳኝ ሰዓት ጥላ ሆኜ ከፀሐዩ ሐሩር የተከላከልኩላችሁ እኔ ነኝ። እኔን የማይረባ ልትሉኝ አይገባም ነበር! እኔ ባልኖር ኖሮ በፀሐዩ ንዳድ ተቃጥላችሁ ትሞቱ ነበር።” በማለት እያዘነ ተናገራቸው።

መንገደኞቹም ያልተገባ ንግግር ተናግረው ዛፉን በማስቀየማቸው አዘኑ። “ይህንን በችግራችን ጊዜ የደረሰልልን መልካም ዛፍ በክፉ ማንሳት አልነበረብንም፣” ብለው ዛፉን ይቅርታ ጠየቁት። ዛፉም ይቅርታቸውን ተቀበለ።

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አራት

**ሀ. ምንባቡን ደግማችሁ አንብቡትና ቀጣዮቹን ጥያቄዎች 'እውነት' ወይም 'ሀሰት' በማለት መልሱ።**

1. በበረሃ ሲጓዙ የነበሩት ሦስት መንገደኞች ናቸው።
2. መንገደኞቹን ከፀሐይ ሀሩር የተከላከለው ዛፉ ነው።
3. የመንገደኞቹ ጉዞ በአንድ የክረምት ወቅት ነበር።
4. መንገደኞቹ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ ጠየቁ።
5. መንገደኞቹ የተጣሉት እርስ በእርሳቸው ነበር።

## ክፍለጊዜ፡ ዘጠኝ

**ለ. ተገቢውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ**

1. "በንዳድ ተቃጥላችሁ ትሞቱ ነበር፣" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. እሱ ባይኖር ብርዱ ይጎዳቸው ነበር ማለቱ ነው።
ለ. ሙቀቱ ከፍተኛ ስለነበር ይጎዳችኋል ማለቱ ነው።
ሐ. በአካባቢው እሳት ተከስቶ ነበር ማለቱ ነው።
መ. በንግግራቸው በጣም ተናድጄ ነበር ማለቱ ነው።

2. "ያልተገባ" ሲል ____________ ማለቱ ነው።

ሀ. የማይጣፍጥ ሐ. ልክ ያልሆነ

ለ. ባለቤት የሌለው መ. ያልተሳሳተ

3. ይቅርታ የጠየቀው ማነው?

ሀ. ዛፉ ለ. መንገደኞቹ ሐ. ፀሐዩ መ. ሀሩሩ

4. "ውለታቢስ" የሚለው ቃል ፍቺ__________

ሀ. የተደረገለትን የሚረሳ ሐ. ብድር የሚመልስ

ለ. ለተደረገለት የሚያመሰግን መ. ውለታ የሚከፍል

5. የምንባቡ መልዕክት__________

ሀ. ጥፋት አጥፍቶ ይቅርታ የለም

ለ. መልካምነት ጥሩ አይደለም

ሐ. ጥሩ ማድረግ ያስቀጣል

መ. በጎ ላደረገ ክፉ አይመለስም

**ክፍለጊዜ፡ አስር**

## ትምህርት አራት፡ ቃላት

### መልመጃ አምስት

**ሀ. 'መንገደኞቹና ዛፉ' ወደሚለው ምንባብ ተመለሱና ሳጥኑ ውስጥ ያሉት ቃላትና ሀረጎች የያዙትን አውዳዊ ፍቺ አመልክቱ።**

| | | |
|---|---|---|
| ማስቀየም | ደረሰልን | የተከላከለልን |
| አይገባም | የማይረባ | አረፍ እንበል |
| በጥሞና | ተቀበለ | በፀሐዩ ንዳድ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አንድ

ለ. በ ‘ሀ’ ስር ላሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ ‘ለ’ ስር እየፈለጋችሁ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አክሳሪ | ሀ. ርካሽ |
| 2. ገገር | ለ. ጭማሪ |
| 3. ቅናሽ | ሐ. ትርፍ |
| 4. ውድ | መ. አዋጭ |
| 5. ኪሳራ | ሠ. ሻጭ |

## ክፍለጊዜ፡ አስራ ሁለት

ሐ.ቀጥሎ በ‘ሀ’ ስር የተሰጡት ቃላት ከላይ ካነበባችሁት ምንባብ የተወሰዱ ናቸው። አውዱን ከግምት በማስገባት በ‘ለ’ ስር ካሉት ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1.ሲደራ | ሀ. በገንዘብ መግዛት |
| 2. አይረሴ | ለ. ውጤት |
| 3.መገበያየት | ሐ. ጥቅም ላይ የሚውል |
| 4.ተዋፅኦ | መ. ሞቅ ሲል |
| 5.መሸመት | ሠ. በሽበሽ |
| 6.ፍጆታ | ረ. የማይዘነጋ |
| 7.እንደልብ | ሰ. መሸጥ፣ መግዛት |
| 8.ገላጣ | ሸ. ያልተከለለ ስፍራ |

9.የተመደበውን ቀ. አመጣጥነው
10.አብቃቅተው በ. የተያዘውን

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ሶስት**

**መ. ተከታዮቹን ባዶ ቦታዎች ተገቢ በሆኑ ቃላት አሟሏቸው።**

1. ለተገኘ አገልግሎት የሚሰጥ ገንዘብ ________ ሲባል፣ ለከፋይ የሚሰጥ ቀሪ ገንዘብ ደግሞ ________ ይባላል።
2. ዕቃ የሚገዛ ሸማች ሲባል፣ ዕቃ የሚሸጥ ደግሞ ________ ይሰኛል።
3. ለዕዳ ከፈልኩ ብል ለዕቁብ ________ እላለሁ።
4. አንድ ነገር ተሸጦ ተጨማሪ ገቢ ከተገኘ______፣
5. አንድ ነገር ተሸጦ የቀድሞ ዋጋውን ካላወጣ ________ ይባላል።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ አራት**

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

### መልመጃ ስድስት

**እነዚህን አረፍተነገሮች ጠቆር ብለው የተፃፉት ላይ ትኩረት እያደረጋችሁ አንብቧቸው።**

1. ስዕል ለመሳል እርሳስ ብቻ ሳይሆን ወረቀትም ያስፈልግሻል።
2. እሷ ቢደክማትም እንኳ የቤት ስራዋን ሳትጨርስ አትተኛም።
3. ሰዓቱ ካልደረሰ በስተቀር ለዕረፍት ከክፍል አንወጣም።
4. እናቴ ከገበያ እስክትመጣ ድረስ ስጠብቃት ነበር።
5. በጊዜ ብትመጣ ኖሮ አርፋጅ አትባልም ነበር።

## መልመጃ ሰባት

**ከላይ ያሉትን የሚመስሉ የየራሳችሁን ሌሎች አምስት አረፍተነገሮች ጽፋችሁ አንብቡ።**

## ክፍለጊዜ፡ አስራ አምስት

## መልመጃ ስምንት

**በ 'ሀ' ስር ያሉትን ጅምር አረፍተነገሮች ተመልከቱና በ 'ለ' ስር ካሉት ማሚያዎች ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1 ፈተናውን ስላለፈ | ሀ. ..ሽልማቷ ይቀመጥላታል። |
| 2 እሷ ብትኖርም ባትኖርም | ለ. …ውይይቱ የሚቀጥል ይሆናል። |
| 3 ቡና በጥራት ሲመረት | ሐ. …መርጠሽ ልትወስጂ ትችያለሽ። |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | የተባልኩትን ብሰማ ኖሮ | መ. …ያሰብንበት ሁሉ እንደርሳለን። |
| 5 | ጊዜን በአግባቡ ስለምንጠቀም | ሠ. …ዛሬ አላዝንም ነበር። |
| 6 | እነሱ ባይመጡም እንኳ | ረ. … በጣም ደስ አለው። |
| 7 | ይህንን ወይም ያንን | ሰ. … የሚያስገኘው የውጪ ምንዛሪም ከፍ ይላል። |

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ስድስት

## መልመጃ ዘጠኝ

**ሀ. በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን አያያዦች በመጠቀም አረፍተነገሮች መስርቱ።**

| | | |
|---|---|---|
| ምንም እንኳ | ብቻም ሳይሆን | እስከ … ድረስ |
| ካልሆነ በስተቀር | ቢሆንም እንኳ | ባል…ኖሮ |

### ክፍለጊዜ፡ አስራ ሰባት

**ለ. የሚከተሉትን አረፍተነገሮች ፃፏቸውና አያያዥ የሆኑት ቃላትና ሀረጋትን አስምሩባቸው።**

**ምሳሌ፡** ምንም እንኳ የደከመኝ ቢሆንም ጥናቴን አላቋርጥም።

1. ሳልማር ብቀር ኖሮ ይቆጨኝ ነበር።
2. ምንም እንኳ ገበያ ቢሄድም የሸመተው ነገር የለም።
3. ወንድሟ ብቻም ሳይሆን እህቷም ታታሪ ናት።
4. ደጋግማ ብትነግረኝም እንኳ ልሰማት አልቻልኩም ነበር።
5. ዛሬ ስላረፈድኩኝ መምህሬ የሚያዝኑብኝ ይመስለኛል።
6. የኮሮና ወረርሽኝ ባይከሰት ኖሮ ትምህርታችን አይቋረጥም ነበር።

**ክፍለጊዜ፡ አስራ ስምንት**

**ተግባር አራት**

**የተለያዩ አያያዦችን ተጠቅማችሁ ስድስት ስድስት አረፍተነገሮች ፃፉ። የፃፋችኋቸውንም ለቡድን ጓደኞቻችሁ በማጋራት ሀሳብ ተለዋወጡባቸው።**